# ሴትነትና እናትነት በፀሐይ መልአኩ ልቦለዶች

*አጋረደች ጀማነህ*

## መግቢያ

### ደራስያትና የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ

ይህ አጭር ቅኝታዊ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ ከአደረጉት ሴት ደራሲዎች መካከል በደራሲ ፀሐይ መልአኩ ሦስት ልቦለዶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ አንድን ነጠላ ጉዳይ መርጦ መነሳት የደራሲዋን የትኩረት መስመር ለማስተዋል ያመቻል በሚል እምነትም ራስን መተካት፣ ትውልድን መቀጠል፣ በሚሉት ዙሪያ የተነሱትን በሶስቱም ልቦለዶች የሚታየውን ጭብጥ በማንሳት ፀሐይ ስለሴትነት፣ በአጠቃላይ ስለሥርዓተ ጾታ ያላትን አቀራረብ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

ልቦለዶቿ ከቀደሙት ደራስያት በተሻለ የአጻጻፍ ቅንብር የተደራጁ መሆናቸው፣ በተለምዶ ቤሳ ልቦለዶች[1] ናቸው ከሚባልላቸው ቀደምት ድርሰቶች የተሻለ ስፋትና ጥልቀት ባህርያቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የምታነሳቸው ጭብጦች ለየት ያሉና ሴትነትን በጥልቀት መርምረው የሚያሳዩ መሆናቸው ለጉልህ አስተዋጽኦዋ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን የመጀመሪያዋ የረጅም ልቦለድ ደራሲ ናት ማለት አለመሆኑን እዚህ ላይ ማስታወስ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በአንድንድ መድረኮች ላይ (ለምሳሌ ህዳር 20 ቀን 2000 በተላለፈ የሬዲዮ የጠቅላላ እውቀት ጥያቄ ፕሮግራም ላይ) የመጀመሪያዋ የረጅም ልቦለድ ደራሲ እንደሆነች ተደርጎ የተላለፈውን መረጃ ማንሳት ይቻላል፡፡ ለዚህም በሚቀጥሉት ገጾች የተጠቀሱት አንዳንድ ቀደምት ሥራዎች ማስረጃዎች ናቸው፡፡

ለየት ያሉ ጭብጦችን በማንሳት ማህበረሰቡን የሳለችባቸው የጸሐይ መጻህፍት የዚህን ጥናት አቅራቢ ትኩረት የሳቡባቸው ተጨማሪ በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ ተደጋጋሚ ገለጻዎች፣ አንድ ዓይነት ሰብእና ያላቸው ገጸባህርያት በየመጻህፍቱ ተደጋግሞ መታየት፣ አጋጣሚዎችን ለገጸባህርያቱ መነሳትና መውደቅ መንስኤ ማድረግ፣ ቂምና በቀል የገጸባህርያት የርስበርስ ግንኙነት መሰረቶች መሆናቸው፣ የአእምሮ ህመምና መደንዘዝ ተደጋጋሚ ክስተት ሆኖ መነሳቱ፣ ጥቂቱ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ ደግሞ ልብ ተብለው ሲታዩ አንድ ዘንግ ላይ የተጠመጠሙ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ሴትነትና እና እናትነት መሽከርከሪያ አውታሮቻቸው ናቸው፡፡ ሴትነትና እናትነት ከኑሮ ስልጣን ባለቤትነት (Powere Relations) አኳያ የወንድና የሴትን ማህበረሰባዊ ሥፍራ ለማየት የሚያስችሉ ማህበረሰባዊ ስፍራዎች ወይም ክፍሎች ናቸው፡፡ ሚሼል ፉኮ ስለየማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ስልጣንና ስለሥልጣን ባለቤትነት ሲገልጽ የተናገራቸው መስፈርቶች ለዚህ ጥናት እንደማእቀፍ ሆነው ያገለግላሉ (ፉኮ፣ 1982)፡፡

በዚህ አጭር ስራ ማየት የተፈለገው ቀደም ሲል እንደተገለጸው የሴቶች ሰብእና በእናትነትና በፍሬያማነት ላይ ብቻ ተተኩሮ መቀረጹ፣ የሴቶች የህይወት መነሻና መድረሻ በእነዚህ ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ኃላፊነቶች መቀንበቡን አንጽሮ ማሳየት ነው፡፡ ይህንንም በማድረግ ደራሲዋ በድርሰቶቿ የሰዎችን ማህበረሰባዊ ስፍራ ተመጣጣኝ ያደረገች ቢመስልም ወይም ደግሞ በባህል ላይ ጥያቄዎቿን ያቀረበችበትን መንገድ መፈተሽ ነው፡፡ የሰዎች የበላይነትና የበታችነት በሥራዎቹ እንዴት ነው

---

[1] ዮሐንስ አድማሱ

የተገለጹት? የበላይትነና የበታችነት (Power Relations) ምንጩ ምንድነው? የበላይነትን ማግኘት እንዴት ይቻላል? ለበታችነት የሚዳርጉ ባህላዊና ልማዳዊ ቅቡልነት ያላቸው የኑሮ ይትበሃሎች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ዝርዝርና ተቀጥላ ሆነው የሚነሱት ጉዳዮች ናቸው:: በዚህ መስመር እናትነትና ሴትነት ከዚህ እንዴት እንደሚያያዝ እንመለከታለን::

ይህን በማጠናትም ሥነጽሁፍ ምን ያህል ተቋማዊ የኃይል ማንጸባረቂያ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ይቻላል::

የሚከተሉት ነጥቦች የዚህ ጥናት ፋይዳ ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ::

1. የፀሐይን ስነጽሁፋዊ አስተዋጽኦ በተለዩ ማሳየት፣
2. እምብዛም በሂሱ መድረክ ሥፍራ ያልተሰጣቸውን የሴቶች ሥራዎች መጠናት ያለባቸውና የተለየ መልእክት ሊያዙ እንደሚችሉ መጠቆም፣
3. ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ እንዲችሉ ለሌሎች አጥኚዎች ጥቁምታ መስጠት፣ የሚሉት ይጠቀሳሉ::

ይህ አጭር ጥናት በሚከተሉት ንዑሳን ርእሶች ላይ ያተኩራል:: አንደኛ ስለጸሃይ መጻህፍት አጭር ማስተዋወቂያ፣ ከዚያም ንድፈሃሳባዊ መሰረት ሊሆን የሚችል አጭር መግለጫ፣ ከዚያም እናትነትና ስነተዋልዶ እንዴት እንደተቀረጸ ማሳየትና በመጨረሻም በዝርዝር መግለጫው የተነሱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የፀሐይን ልቦለዶች ልዩ ባህርያትን ማሳየት ነው::

ስለፀሐይ መጻህፍት ጥቂት የጥናት ሥራዎች ቢኖሩም አሁን ማየት በተፈለገው አቅጣጫ የተመለከተ ሥራ ግን አላጋጠመኝም:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ይህ ሥራ ከሚያተኩርበት አቅጣጫ ባይሆንም ለዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥቂት የመመረቂያ ሥራዎችን ለአብነት መጥቀስ ተገቢ ነው::

በዓለም ባየልኝ በ1984 የተጻፈው «ሴቶች በሴቶች ደራስያን ዓይን» የሚለው ሥራ በቀዳሚነት ይጠቀሳል:: ይህ የመመረቂያ ጽሁፍ በቀረበበት ዘመን የነበረው የጸሐይ ልቦለድ ድርሰት <u>ቋሳ</u> ብቻ ስለነበር ይህንኑ ድርሰት ከየምወድሽ በቀለ <u>የባከነ ጊዜ</u> ልቦለዶች እና ከጀማል ሱሌይማን ጋር በጋራ ባሳተመቻቸው መድበሎች ማለትም <u>የተሸጠው ሰይጣን</u> እና <u>ያልተመቻት ችግኝ</u> ውስጥ ከሚገኙ የየዝና ወርቁ አጫጭር ልቦለዶች ጋር ሴቶች ገጸባህርያት እንዴት እንደተሳሉ በንጽጽር ያጠናችበት ሥራ ነው::

አሰፋ ወርቁ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው የመመረቂያ ሥራም እንደዚሁ ሁለቱን የጸሐይን ልቦለዶች ከሌሎች ሴቶች ደራስያን ጋር በጅምላ የመረመረበት ነው:: አሰፋ ትኩረት ሰጥቶ የተመለከተው የአጻጻፍ ቴክኒኮችን ነው፣ ከ1959 እስከ 1985 ዓ.ም የጻፉና ያሳተሙ ሴቶችን ልቦለዶች በመውሰድ:: በፀሐይ ልቦለዶች ለታሪክ ማዳበሪያነት ከዋሉት መካከል የስልክ አጠቃቀም ዋነኛው መሆኑን አንስቷል::

አሰፋ በሥራው ካካተታቸው ነጥቦች አንዱ በህይወት ካሉ ደራስያት ጋር ቃለመጠይቅ በማድረግ ሀሳባቸውን ማስፈር ነው:: በቃለመጠይቁ ፀሐይ ስለራሷ ከሰጠቻቸው ገለጻዎች መካከል ሥእል መሳልንና የልብስ ስፌትን እንደምትሞክር፣ በሙያዋ መምህርት እንደሆነች፣ ስትጽፍ አበባ ከፊቷ እንደማይለይ፣ በጽሞናዊ ስራዋ ወቅት ብራንዲ መጎንጨት እንደሚያስደስታት፣ የሁለት ልጆች እናት ብትሆንም በመሰረቱ በህጋዊ ጋብቻ እንዳልታሰረች የገለጸችው ይገኝበታል::

በአሰፋ ጥናት የተነሱት አንዳንድ ነጥቦች በዚህ ጽሁፍ ተደጋጋሚ ተብለው የተነሱ መልእክቶችና ገለጻዎች የደራሲዋ የግል ተሞክሮዎች መሆናቸውን፣ እነዚህ ግላዊ ተሞክሮዎቿ በሥራዋ ላይ እንደሚንጸባረቁ ፍንጭ በመስጠት ረገድ አስተዋጽኦ

አድርጓል፡፡ ለምሳሌ በልቦለዶቿ ውስጥ ሁሉ የመምህርነት ሙያ እጅግ ተወዳሽና ክቡር ሥራ መሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተጠቅሷል፡፡ መምህርነት የበጎ ምግባር መግለጫም ነው፡፡ ነጠላ እናትነትም እንደዚሁ የጠንካራ ሴት ገጸባህርያቷ መገለጫ ሆኖ ቀርቧል፡፡

## ትወራዊ መነሻ

### *ስለኢትዮጵዊያን ሴቶች ደራሲዎች ማስተዋወቂያ*

ስለሴት ደራስያን ስራዎች ቅኝታዊ ጥናት ማድረግ የጀመርኩት ገና ያኔ ለመጀመሪያ ዲግሪ መመረቂያ በጻፍኩት ወረቀት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ለጥናት መረጃ ሳሰባስብ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል ጎልተው የሚጠቀሱት በሴቶች የተጻፉ ድርሰቶች መኖራቸውን አለማወቅ፣ ቢታወቁም እውቅና አለመስጠት የማስታውሰው ሁኔታ ነው፡፡ አንድን የስነጽሁፍ ስራ ገምግሞ ደካማና ጠንካራ ጎኑን መዝኖ ከሌሎች መሰል ሥራዎች ጋር ሲነጻጸር ሚዛን የማይደፋ ከሆነ ያንኑ በማሳያ አስደግፎ ማስረዳት ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሥራዎቹ እያሉ፣ በሥራዎቹም ላይ በደራሲነት የተጠቀሱ ስሞች እያሉ በደራሲነት የተጠቀሱት ሴቶች በእርግጥ የድርሰቱ ባለቤቶች ላይሆኑ ይችላሉ፣ የሚለው ማጣጣያ አመለካከት ግን ለአስተዋጽኦዋቸው እውቅና አለመስጠት መሆኑን ከማስረገጥ ውጪ ሌላ መልስ ሊገኝለት አይችልም፡፡ በመሆኑም ሴቶች በፈጠራ ድርሰት ደራሲነት ለሥነጽሁፍ እድገት በተለይም በዝርው ድርሰት ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉና በማድረግም ላይ መሆናቸውን ለማሳየት ሲባል የተዘጋጀ ነው ይህ ጥናት፡፡ ይኼ መሠረታዊ መነሻዬ ነው፡፡

ከሣራ ወርቅነህ *ማዕበል* የሼክስፒር ድራማ ትርጉም (1933)፣ እና ከስንዱ ገብሩ *የልቤ መጽሀፍ (1942)*፣ (እነዚህ በድራማ ዘርፍ ናቸው) አንስቶ እስከ 1970 ማጠቃለያ አመታት ድረስ ብዙ የሴቶች ሥራዎች ለህትመት በቅተው እንደነበር በህትመት ያሉት ስራዎች ይመሰክራሉ፡፡  የመቅደስ አስናቀ *መሃጀባ (1966)*፣ የእየሩሳሌም ይስማው *ብሩህ ህሊና በቀና ጎዳና*፣ የመጠነወርቅ ሳሙኤል *የባከነው ጊዜ* (1965) የተሰኙት ቤሳ እና ረጃጅም ልቦለድ መጻህፍት ይጠቀሳሉ፡፡

ወደ 1970ዎቹ አመታት ስንመጣ በኢትዮጵያ ዘመናዊ አጭር ልቦለድ ጽሁፍ የመጀመሪያዋ ሴት የአጭር ልቦለድ ደራሲ የዝና ወርቁ በጥምር ደራሲነት (*የተሸጠው ሰይጣን 1978*) ብቅ አለች፡፡ ከእርሷ በመቀጠል ደግሞ ጸሐይ መልአኩ የመጀመሪያውን ረጅም ልቦለዷን በ1982 አሳተመች፡፡ ከዚያ በኋላ ፀሐይ ብቻ ሳትሆን በርካታ ሴት ደራስያን በተለያዩ የሥነጽሁፍ ዘውጎች ሥራዎቻቸውን ይዘው ከህዝብ ተገናኝተዋል፡፡

ፀሐይ መልአኩ ሦስት ረጃጅም ልቦለዶችን ጽፋለች፡፡ ቋሳ በ1980፣ አንጉዝ በ1994፣ ቢስ ራሔል ደግሞ በ1996 ታትመዋል፡፡ በዚህም በመነሻዬ ላይ እንደፎቀስኩት በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ታሪክ ከሴት ደራሲዎች ጎራ የቀዳሚነቱን ሥፍራ ልትይዝ የበቃች ነች ማለት እደፍራለሁ፡፡

### *የባህልና የሥነጽሁፍ ግንኙነት ምንድነው?*

ፀሐይ በልቦለዶቿ ውስጥ የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮችን ነው የሳለችው፣ ምንም እንኳን ማህበረሰባዊ ችግሮችን መለያ መንገዶች የተለያዩ እና ይህም ተግባር ቀላል ባይሆኑም (Hilgartner & Bask: 1988)፡፡

ሚሼል ፉኮ ከእርሱ ጥናት በፊት የታዩ በሃይል (Power Relations) ላይ የተመሰረቱ ማህበረሰባዊ የርስ በርስ ግንኙነቶች

አራት አይነት መሆናቸውን ሲገልጽ አንዱ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያሳዩት የበላይነት መሆኑን ጠቅሷል (Foucault, 1982:212)::

ባህል የሰዎች የአኗኗር ስልት ነው:: የሰዎች የአኗኗር ስልት የሚገለጽበት ባህል በተለያዩ ገጽታዎች ሊንጸባረቅ ይችላል:: ለምሳሌ የጋብቻ አመሰራረት፣ የልጆች አስተዳደግ የማህበራዊ ግንኙነት ስርአት ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ስነጽሁፍ ደግሞ ይህንን የማንጸባረቅ ኃይልም ሥልጣንም አለው (Englstad, 2003: 112, Wendy, 1998):: ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ባህል ያሉትን ጠንካራና አሉታዊ የኑሮ ገጽታዎች ማሳየት ብሎም ለውጥ እንዲፈጠር፣ መሻሻል እንዲከተል ወይም ደግሞ ያለው ባህላዊ ገጽታ ጸንቶ እንዲቆይ የማድረግ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል ስለዚህ ስነጽሁፍ የሃይል መገለጫ ተቋም፣ ደራስያን ደግሞ የዚህ ኃይል ባለቤቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: በተለይ በማህበረሰባቸው ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው ደራስያን የለውጥ ሀዋርያት ሊሆኑ ሲችሉ ተቀባይነት የሌላቸው ደግሞ ምናልባትም ጉልበታቸው እምብዛም ውጤትን ላያመጣ ይችላል (Engelstad, 2003:113-114)::

ባህል በሰዎች የርስ በርስ ግንኙነት ወቅት የሚፈጠሩ የበላይነትንና የበታችነትን ሊያጸና ወይም ሊያመላክት ይችላል:: የበላይነት ማለት ላሞን እንደሚለው «ሊከተል የሚችልን ማናቸውንም የመቋቋም ሙከራ በመጨፍለቅ የራስን ፍላጎት በሌሎች ላይ የመጫን ችሎታ ነው:: ይህንንም ማድረግ የሚቻለው አበረታችም ሆነ አሉታዊ ማነቃቂያን በመስጠት ይሆናል» (Lamnot, 1989:133)::

የበላይነትን ማሳየት ማለት በሁለት መልኩ ሊከሰት ይችላል:: ይኸውም ቀጥታ (Direct Power) የሆነና ቀጥታ ያልሆነ (Indirect Power) በሚል ይከፈላል:: የመጀመሪያው የሁለቱ ወገኖች ግንኙነት አንዱ በአንዱ ቁጥጥርና ተጽእኖ ስር የሚውልበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪውን ያህል ባልጠነከረ መልኩ አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበትነው:: አንዱ ወገን በሌላው ላይ የሚኖረው ተጽእኖ መሰረቱ የሚፈልገውን ነገር መፈጸም የሚያስችሉት ቅድመሁኔታዎች ሲኖሩ፣ የምጣኔ ሀብትም ሆነ የማህበረሰባዊ ስፍራው የሚፈልገውን ማድረግ የሚፈቅድለትን ስልጣን ሲያጎናጽፈው ነው::

ሌላውን ወገን ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርጉት ሁኔታዎችም እንዲሁ:: ለምሳሌ ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይነት አላቸው ሲባል ሴቶችን መጠቀሚያ፣ ታዛዢቸው እንዲሆኑ የሚያስገድዱ አጋጣሚዎች መፈጠር አለባቸው ማለት ነው:: ለምሳሌ የንብረት ተቆጣጣሪነት፣ የሥራ እድል ማግኘትን፣ በትዳር ወቅት የመምረጥና የማስገደድ መብትን ባህሉ ለወንዶች የሚፈቅድ ከሆነ ሴቶች እነዚህ የሃይል ምንጮች ስለሌሏቸው የወንዶች ጥገኞች መሆናቸው ግድ ነው::

በአንጻሩ ደግሞ ሴቶች ኢኮኖሚ ያሻቸዋል:: ትዳር መያዝ ማህበራዊም ተጀፐረቲም ጥሪ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: መኖር ይገባቸዋል:: ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ማግኘት የሚችሉት ባህሉ የባለቤትነት ሥልጣንን ላጎናጸፋቸው ወንዶች ጥገኛ በመሆን ነው (Lamont, 1989:133)::

ሥነጽሁፍ እውነታን ያንጸባርቃል ከተባለ በውስጡ የሚነሱ ጉዳዮች የሰዎችን የእርስበርስ ግንኙነት ማሳየት፣ ይህንን መሰረት ያደረገ የማህበራዊ ለውጥ ትግል ወይም ማህበራዊ ኑሮ ዘለቄታን ማጽናት ነው:: ደራስያንም በእውነታው የሚታዩ የበላይነትና የበታችነትን ገጽታ መነሻ ያደረገ ግጭትን በማጧጧፍም ለልቦለዶቻቸው ታሪክ ግስጋሴ ጥሩ ስልትን ይቀይሳሉ:: በፀሐይም ስራዎች ውስጥ የሚታየው በአብዛኛው በጾታ ጦርነት የተተገነ ማህበራዊ ግጭት ነው::

## ማህረበሰባዊ ኃላፊነትና ማህበረሰባዊ አመለካከቶች

በፀሐይ ልቦለዶችም ውስጥ የበላይነትና የበታችነት አለ:: ይህን የበላይነትና የበታችነት የፈጠሩት ምጣኔ ሀብታዊ ባለቤትነት፣ ሰፍኖ ያለ ማህበረሰባዊ እምነትና ልማድ፣ ፖለቲካዊ ስርዓት የመሳሰሉት ናቸው:: የግጭቶቹም መነሻ የበታች የሆኑት (ሴቶች) ጫናቸውን ለመቋቋም ህልማቸውን እውን ለማድረግ የሚያደርጉትን መፍጨርጨር እናያለን:: ከተሰጣቸው ባህላዊም ሆነ ተፈጥሯዊ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች አንጻር የሚሹትን ለማግኘት የተጠቀሙባቸውን ስልቶችም እንመከታለን::

ማህበረሰቡ የሚያምንበትና የተቀበለው ነገር ይኖራል:: ይህን ቅቡል የሆነ ወግና ሥርዓት በማህበረሰቡ አባላት የእርስ በርስ ግንኙነትና ማህበረሰባዊ ተቋም በሆነው ትዳር ጥምረት በሚቀጥለው ትውልድ ላይ ለማተም ይፈልጋል:: በልቦለዶቹ ውስጥ የተሳለው ቀጣይ ትውልድ ደግሞ የተበተነ፣ ሰብሳቢ ያጣ የማንነት ጥያቄ ያንዣበበት፣ በተፈጠረው የማህበረሰባዊ ተቋም ልልነት  ሳቢያ የጠበቀ የወላጅና የልጅ ግንኙነትን በማጣቱ ሳቢያ ሰብእናው የተናጋ፣ ነው የሆነው::

ህብረተሰቡ በሰጣቸው ሥፍራ የበታችና እምብዛም ክብርና ትልቅነት የሌላቸው ሰዎችን የሚወክሉ ገጸባህርያትም አሉ:: ነገር ግን እነዚህ ገጸባህርያት ዞረው ዞረው የበላይነትን ሲያገኙ ስፍራና ዝናን ሲጎናጸፉ ይታያሉ:: ከበደ ጋሪ በጋሪ ነጂነቱ ይገለሳል:: በአብዮተኛነቱ ይገለሳል:: ጠንካራ ሰራተኛነቱ አይደለም የታየው:: እነሰናይት በልጅነት አእምሯቸው ጋሪ ነጂ ሆኖ እርሷን ለጋብቻ መጠየቁ ያናድዳቸዋል:: አንድም በጋሪ ነጂነቱ ከዚህም በላይ ደግሞ የአበራ እስጢፋኖስ ፍቅረኛ በመሆኑዋ:: ልጆቹ ለከበደ ያላቸውን አመለካከት ከየት ወረሱት? ከቤተሰብ:: ለየት ያለ የሚሆንብን ግን ለምን የሰናይት አባት አቶ ብሩ ሠናይትን ሊድሩለት እንደፈለጉ ነው::

*የሴቶች አቀራረጽ*

የልቦለዶቹ ሁሉ አበይት ገጸባህርያት ሴቶች ናቸው:: ሴቶቹ የሚያጋጥሟቸው ግጭቶች ደግሞ ባህላዊና ፖለቲካዊ ገጽታ አላቸው:: በአንዱ ወገን የእነዚህን ሴቶች ሰብእና የሚያጎድፉ፣ ህሊናቸውን የሚያደሙ፣ በእንቅፋትነት የሚጋረጡ ወንዶች አሉ:: ለምሳሌ ምንተስኖትና ውብሸት፣ ፋናዬ እና መቶ አለቃው በ<u>ቋሳ</u>፣ ሠናይትና ከበደ ጋሪ በ<u>አንጉዝ</u>፣ ተስፋዬ ቦሩ እና ኤፍሬም በአንድ በኩል፣ ራሔል በሌላ በኩል ሆነው ሲፋለሙ የሚታዩት ገጸባህርያት በ<u>ቢስ ራሔል</u> ይጠቀሳሉ::

የተቃራኒ ጾታ ተጽእኖ ብቻ ሳይሆን ባህልና ልማድም ጠንካራ ክንዶቻቸውን በሴቶች ላይ ሲያሳርፉና ሃያል እንግልት ሲያስከትሉባቸው ይስተዋላል:: ለምሳሌ ራሔልና ቤተሰቦቿ ከዘር የሚወራረስ የአካል ጉዳት ወይም የሥጋ ደዌ ህመም «ጣጠኞች» ናቸው ይባላሉ (ገጽ 24):: በዚህም በአካባቢያቸው ነዋሪዎች ለዚያውም በቅርብ ወዳጆቻቸው ይገለላሉ:: ስለዚህ ሴቶቹ ገጸባህርያት ህይወት ለፈተና የምታጋልጣቸው በጾታ ተቃራኒዎቻቸው ወንድኛ ፍላጎት በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በህብረተሰቡ አጉል አመለካከት ሳቢያ ነው:: በእርግጥ የፊተኛው በሁለተኛው ውስጥ የተካተተ ሊሆን ይችላል:: የሰዎች ማህበረሰባዊ ስፍራ በማህበረሰቡ አመለካከት መሠረት ይወሰናልና::

ከጾታ ተቃራኒዎቻቸው በኩል የሚመጣውን ተቃርኖ ለመፍታት ደግሞ ከሁሉም በላይ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሌሎች ወንዶች አሉላቸው ሴቶቹ:: ዞሮ ዞሮ ምንም ቢፍጨረጨሩ የወንዶች እገዛ ያሻቸዋል ማለት ነው:: ይህ ሁኔታ ግን በተቃራኒው ለወንዶች የማይሰራ መሆኑን ልብ ይሏል:: ለምሳሌ

ለምንተስኖት መኩሪያ፣ ለፋናዬ የዩኒቨርሲቲ ተመራማሪው ወጣት፣ ለሠናይት ግርማቸው ወ/ኪዳን እና ለራሔል ደሳለኝና ጌታሁን ከአገር ውስጥ፣ ጀምስ ዊሊ ደግሞ ከአገር ውጪ:: እነዚህ ሁሉ ግን ድጋፋቸውም ሆነ አለኝታነታቸው አንድም ስለሴት ብዙም ደንታ የሌላቸው (ደሳለኝና መኩሪያ) ወይም በሰብአዊነት የተሟሸ ሰብእና ያላቸው ወንዶች (ፋናዬን አስተምሮ ለወግ እንዳበቃት የዩኒቨርሲቲ ተማሪውና በኋላም መምህር፣ እንዲሁም ባለትዳር የነበረው ቅኑ ጌታሁን) አለያም ደግሞ በተገንነት የሚያነሷቸውን ሴቶች ሴትነት የኋላ ኋላ ተጠቃሚ የሚሆኑ (ጀምሲ ዊሊ) ናቸው::

የመውደድ የመጥላት የበቀል ሽክርክሪት ነው ልቦለዶቹ የሚያሳዩት:: የልቦለዶቹ መሰረት ፍቅርና ወዳጅነት ሆኖ መጨረሻው ግን በቀል ነው:: ፍቅር ቅናት በቀል:: ለምሳሌ ምንተስኖት ከዘመናት የአልጋ ቁራኛነት ከዳነች በኋላ ህልምና እቅዷ የሚሆነው ለዚህ የዳረጋትን የልጇን አባት ውብሸትን ለመበቀል መመኘት ነው:: ነገር ግን ውብሸት ራሱ በህሊና ጸጸትና በድንጋጤ ለእድሜ ልክ ሽባነት ይዳረጋል:: በመጨረሻ ነው ጥፋትና በደሉ የሚታወቀው፣ ለይቅርታ መነሳት የሚታየው::

ሠናይት ከበደ ዋሚን ትበቀላለች:: በቀሏ ግን በፍቅር ሽፋን ነው:: አስቀድማ ሴትነቷን በገጸበረከትነት ታቀርብለታለች:: ለአመታት ውስጡ ተቀብሮ ለነበረው ብሎም ቤተሰቦቿን በበቀል ጥቃት እንዲያጠፋ ላነሳሳው ምኞቱ ትገዛለች:: ከበደ ጋሪን ታገባዋለች:: የአባቷ ገዳይ መሆኑን እያወቀች፣ የወንድሞቿ አጥፊ መሆኑ ተነግሯት ለጋብቻ ትስማማለች::

ሠናይት በሁለት ወገን የህሊና ሙግትና ውጥረት ውስጥ ትገባለች:: በአንድ ወገን ያባቷን ገዳይ በማግባቷ ጓደኞቿን ታጣለች፣ የሚያከብሯትን ሰዎች ፍቅር ታጣለች:: በከበደ ደሴት ቤት ውስጥ ብቻዋን ትሆናለች:: በሌላ በኩል ደግሞ ከደመኛዋ ጋር አብራ መኖሯ ራሱ የህሊና ቁስል ነው የሚሆንባት:: ነገር ግን ለዓላማ ስለሆነ ይህንን ሁሉ ተቋቁማ ትዘልቃለች:: ይህንን ተቋቁማ ስናገኛት ለዓመታት በህመም የቆየ አእምሮ የነበረባትም አትመስልም::

በጎጆ ጥላ ስር አብራ ከሆነች በኋላ ብድርዋን ልትመልስ፣ የአባቷን ገዳይ፣ የወንድሞቿን አጥፊ ልትበቀል እንደምትችል ይሰማታል:: ሰናይት ከበደን የሚያክል ባላጋራ ለመጣል በትዳር ስር መተሳሰር ነበረባት:: አለበለዚያማ ምን ጉልበት አላት? በሰናይት ተሞክሮ እንደምንረዳው ትዳር የመፈቃቀርና በኑሮ መመሳሰል ብቻ ሳይሆን ስውር ጥላቻ ላበቀለው በቀልም አመቺ መንገድ ሆኖ ማገልገሉንም ጭምር ነው::

ሴትነቷ ብቻ ነው ከበደን የታየው:: ሚስት ከሆነች በኋላ ሴት ታዛዥና ተገዢ እንጂ በራሷ የህሊና ምሪት የምትኀዝ አትመስለውም:: ባህሉና ወጉ ያንን አይነት ሰብእና ስፍራ አልሰጠውምና ባይጠብቅ አይፈረድበትም:: ስለሆነም ሳይጠረጥር በወጥመዷ ይገባል::

ራሔል ተስፋዬንና ኤፍሬምን ትበቀላለች:: ሁለቱም በሰብእናዋ ላይ የተረማመዱባት፣ በፍላጎት ማሚያነትና በማግለል በሽታ የረመረሚት ናቸው:: ኤፍሬም የስጋደዌ በሽተኛነቷን ሲሰማ በግልጽ ለመነጋገርም እድሉን ሳይሰጣት ያገለላት፣ በቁራጭ ወረቀት ደብዳቤ ትቼሻለሁ ብሎ የተዋት ነው:: ተስፋዬ ደግሞ የልጅነት ላህይዋን አይቶ እንደብዙዎቹ ተስፈኛ ወጣት ሴቶች በስራ አስገባሻለሁ ድለላ (በእነደሳለኝ አገላለጽ) ሊያነውራት፣ ሊዝናናባት ሲል ደርሰው ያስጣሉት ነው:: ስለሆነም ተስፋዬን፣ ራሷን ሆና ትልቅ ደረጃ በመድረስ የእርሱን እገዛ ሳትሻ

በራሷ ጥረት ከትንሽ ተነስታ አንቱ ለመባል በመብቃት፣ ኤፍሬምንም «ቆማጣ» አለመሆኗን በጊዜ ሂደት በማሳየት የተሰጣት የሀሰት ስም ዝናና ትልቅነትን ከመላበስ እንዳልገታት በማሳየት ትበቀላቸዋለች:: በመሠረቱ በነራሔል ላይ የተወራው ወሬ ሀሰተኛ፣ በቅናት ሰበብ የተለጠፈባቸው መሆኑ በታሪኩ ጎልቶ ወጥቷል::

ኤፍሬም እርሷን ቢንቃትም በመንግሥት ሹምነቱ ስራዋን መርቆ ሊከፍት በመጣ ጊዜ ትከሰትለታለች:: በቀሷ ትልቅ ሰው በመሆን፣ ለሌሎችም ተስፋና መከታ በመሆን ነው:: ተጋጣሚዎቿን ህሊናቸውን በሚመታ የወቀሳ ዱላ በመምታት::

አሰለፉች በዳኜ መኩሪያን የሠርጉ እለት አጥፍታው ትጠፋለች (<u>*አንጉዝ*</u> 1984):: መነሻው በልጅነት አእምሮዋ በተቀረጸው የአገባሻለሁ «ቃል ኪዳን» ነው:: የህጻን አእምሮዋ ቀልድና ምርን መለየት አላስቻላትም:: መኩሪያ የጎረቤታቸውን ልጅ አሰለፉችን «ሚስቴ ነሽ፣ ስታድጊ አገባሻለሁ» ይላት የነበረውን ይዛ አደገች:: እርሷ ህጻን ሆና የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበረው መኩሪያ ቀልዱን በቀልድነቱ እንጂ፣ በልጅ ማጫወቻ ዜማነቱ እንጂ በዘላቂ ሀሳብነት በአእምሮው አልተጻፈም:: ነገር ግን አሰለፉች ህሊናዋ ውስጥ የተቀረጸው ሴት ልጅ አድጋ መጨረሻዋ ትዳር መያዝ ነው የሚለው ማህበረሰባዊ አመለከከት ነው:: እናም የዚያን ጊዜውን ቀልድ የምር አድርጋ ስትጠብቅ ኖረች:: ቃል ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ለበቀል ተነሳች:: ከዚህ መውሰድ የሚቻል ትምህርት አለ:: የማይፈጸምን ተስፋ በህጻናት አእምሮ ውስጥ አለማስቀመጥ::

የበቀልና የቂም መወጣጣት ነው ጎልቶ የሚታየው:: የጾታ ጦርነት ነው ሰፊውን ስፍራ የያዘው፣ በፍቅር ሳቢያ፣ ሴትነትን ለወንድ ፍላጎት መከወኛ ከማድረግ በመነጨ ሩጫ ሳቢያ::

ተመሳሳይ ጾታ ባላቸው ገጸባህርያት መካከል ያለው ጸብ በጾታ ተቃራኒ በሆኑት መካከል እንደሚደረገው ጸብ የከረረና ለጥፋት የሚዳርግ አይደለም:: ለምሳሌ በሴቶቹ መካከል ያለው ጸብ ውስጥ ውስጡን በመሄድና በፍርሃት የታጀበ ነው:: ዘመናይ አረጋሽን በመርዝ በተቀመመ ቅራሪ ለማጥፋት መሞከር:: ቀለሟ ከአክስቷ ጋር ሆና በጓደኛነት ሽፋን ውስጥ ውስጡን ወሬ በማናፈስ የራሔልን ሰብእና ማጉደፍ በቂ ምሳሌዎች ይሆናሉ::

ጸብ ሥር ሰዶ ወደ መጠፋፋት የሚያደርሰው የወንዶች እጅ ሲኖርበት ነው:: ለምሳሌ የነራሔል ሰርግ ላይ የመርዝ ድግስ መሰናዳቱ ተስፋዬ ቦሩ ተጨምሮ የገንዘብና የጉልበት ድጋፍ በማበርከቱ ነው::

ተስፋዬ ብቻ ነው ጌታሁንን እንዲሁም ደሳለኝን በተወሰነ ደረጃ ሊበቀላቸው የሚሞክረው:: መጀመሪያው የበቀል ርምጃ በጉልበት መፈታተሽ ነው፣ መደባደብ:: ቀጥሎ ግን ጊዜን ተገን አድርጎ ከዱላ ባለፈ እርምጃ መጠላለፍ ነው:: ለምሳሌ ጌታሁንና ተስፋዬ ቢሮ ውስጥ ከተደባደቡ በኋላ ጊዜ ተስፋዬ በጌታሁን ትዳር ክፍተት ሲፈጥር ሚስቱን አግብቶ ስሜቱን ለማሳመም ይጥራል:: ጥልቀት ባይኖረው ቢሮክራሲን ተጠቅሞ ጌታሁንን ለማጥቃት እንደሚሞክርም ጥቁምታ ተሰጥቶናል::

በተመሳሳይ መኩሪያና ውብሸት በድብድብ ተጋጭተዋል:: ጓደኝነታቸውም ከዚያን በኋላ ተቋርጧል::

*ሥነተዋልዶ- የተለየ ኃላፊነት*

ፍቅር ባለበት መጸነስ አለ:: ልጆች ይወለዳሉ:: የሚወለዱት ልጆች ደግሞ ሊያድጉም ሳያድጉም ይችላሉ:: ሊወለዱም ሳይወለዱም ይችላሉ:: ከነጭራሹም ሊጨነግፉም ይችላሉ:: ለድህነት፣ ለቤተሰብ መፍረስ፣ ለራስ ወዳድነት መሠረቱ

ወንዶቹና ሴቶች በሚፈጥሩት ጥምር ወዳጅነት፣ በዚህም ወዳጅነት ሳቢያ በሚመጡት ህጻናት ነው።

ይህንን ነጥብ በምሳሌ እናጉላው። ማርታ ለበቀል ብላ ከቀረበችውና ኋላም ለማግባት ከምትወስነው ከተስፋዬ፣ ከጋብቻቸው በፊት ትጸንሳለች። ከጌታሁን እንድትፋታ፣ ከመደባቸው ውጪ የሆነው ጌታሁን የማይመጥናቸው መሆኑን ደጋግመው በመግለጽ ከእርሱ ተፋትታ እርሳቸውን የሚመጥን፣ እርሳቸው የሚደግፉት ባል እንድታገባ ወ/ሮ ሺማጫሽ ልጃቸውን ማርታን ሲወተውቷት ኖረው ከብዙ ጊዜ ንትርክ በኋላ ይሳካላቸዋል።

ጌታሁን ብቸኛ (ደፊፊ አልባ) የሆነችውን የመስሪያ ቤት ባልደረባውን የሽታዬን ልጆች በርህራሔ በመንከባከቡና የችግሯ ድጋፍ በመሆኑ የተነሳ ዲቃላ ልጆቹ እንደሆኑ በተናፈሰው ወሬ ትዳሩ ለመፍረስ ይበቃል። አለነገር ከሴት ጋር አግባብ አልፈጠረም በሚል አመለካከት። ለዚህ ወሬ ጉልበት ማግኘት ደግሞ የማርታ ቤተሰቦች ከጌታሁን በመጋባቷ አለመደሰታቸው አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ መሃል ነው ተስፋዬ ተገኝቶ ለአዲስ ትዳር ማርታ የተገፋፋችው። ከጋብቻቸውም በፊት ለመጸነስ የበቃቸው። ተስፋዬ ደግሞ ከጌታሁን በሁለት ምክንያቶች ቂም ይዟል። አንዱ ራሔል ስለተከላከለበት ሲሆን ሌላው ደግሞ የጌታሁን የሂሳብ ተቆጣጣሪነት በሥራው ስላለተመቸው ነው።

ከማርታ ያቀዱት ጋብቻ ዳር ሳይደርስ ግን ይቅር ጌታሁንን ይቅርታ ጠይቃው ማርታ መመለስ ትወስናለች። ለዚህ ደግሞ አሁንም በማርታ ውስጥ ያለ ጽኑ ፍቅርና የጌታሁን ሆደሰፊነት ድርሻ አላቸው። ጽንሱ ምን ይሁን? ሲባል ጌታሁን «የሚወለደው ህጻን ያለጥፋቱ መንገላታት አይኖርበትም። አንቺም የእናትነት ስሜትሽ እንዲጎዳ አልፈልግም» (ቢስ ራሔል፣ ገጽ 326) ብሎ ይስማማል።

ከሁሉም ውጥን በፊት ግን የማርታ ሞት ይቀድማል። ማርታ በጥርስ መመረዝ ሳቢያ ስትሞት ያ ማንነቱ ለአደጋ ተጋልጦ የነበረው ጽንስም በዚያው ይጨናገፋል።

ፋናዬ (<u>ቋሳ</u>) ለህይወቷ መጨለምም ሆነ ለህይወቷ መለምለም መንስኤ የሚሆነው መጸነሷ ነው። በአንድ መቶ አለቃ ተታላ ተደፍራ የወለደቻቸው መንታ ህጻናት በተላላፊ በሽታ ተለክፈው፣ በድህነቷና በመገለሏ ሳቢያ ሞተውባት፣ ለዚያ ሁሉ መከራ ያበቃትን መቶ አለቃ ለመበቀል እንደተመኘች ስትኖር በመኩሪያ አማካኝነት አስተሳሰቧ ይቀየራል። ከመኩሪያ በፊት ስሙ ባልተገለጸው ገጸባህርይ አጋዥነት በነርስነት መመረቋና በዚሁ ስራ መሰማራቷ መታወቅ ይኖርበታል።

ለበቀል ያላት ምኞት ወደእርምጃ ሳይሸጋገር ይቀራል። ለነገሩ ያንን መቶ አለቃ ለመበቀል ብትሞክር የታሪኩ አካሄድ ሊቀየር እንደሚችል ከታሪኩ አካሄድ ማየት ይቻላል። በልበለዶቹ ውስጥ መኮንንነት ከዚህ አጋጣሚ በስተቀር የአገር ፍቅር ተምሳሌት፣ የጀግንነት ምሰሶ፣ ተናፋቂ ሰብእና ሆኖ ነውና የቀረበው። ይህ አቋም በ*አንጉዣ*ና በ*ቢስ ራሔል* ነጥሮ ተንፀባርቋል። የፋናዬ አጋጣሚ በዚያው መጨለሙ ምክንያታዊነቱ ይገባናል። ለምሳሌ ኮሎኔል ጅግሣ በጠንካራዋ ገጸባህርይ በቅድስት (የተማረችና በራሷ የምትተማን) የተወደደ እና የልጇም አባት ለመሆን የበቃ ነው። የሽታዬ ልጆች አባትም የጦር ሜዳ ፋኖ ነው። ታዲያ በዚህ መካከል እንድምን ፋናዬ ህልሟ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? በምንስ መንገድ የአገር ተከላከይን ተበቅላ ከእግሯ በታች ታደርጋለች? ቀደም ሲል ወጥነትና ተደጋጋሚነት ያላቸው የታሪክ አጽቆች በደራሲዋ ሥራዎች መታየታቸው መገለጹን ልብ ይሏል።

ወደፋናዬ ፍጻሜ እንመለስ:: ከመኩሪያ ትግባባለች:: የስምምነታቸውም ማሰሪያ የሆነውን ፍሬ ጸንሳ ነው ለመሰረግ የበቃቸው:: ይሁን እንጂ የሰርጉ እለት መኩሪያ ይገደላል:: የነጠላ እናትነት እጣ ከፊቷ ተደቅኖ እናስተውላለን::

ሠናይት አንጉዝ ውስጥ ለበቀል እንዲመቻት ካገባችው ከከበደ ጋሪ ትጸንሳለች:: እቅዷ ያባቷን ገዳይ አድብታ መግደል እንጂ በልጅ እታሰራለሁ የሚለው ስላላሳሰበት በመቀደሟ እያዘነች ወደ ውጥኗ ትገሰግሳለች:: ከእናትነት በፊት ያለባትን አደራ ለመወጣት ስለተነሳች የእናትነት ውጥን በራሱ ጊዜ መፈጠሩ ወደ ኋላ አልጎተታትም:: ባደረገችው የአጥፍቶ መጥፋት ሙከራ በጓደኞቿ አማካኝነት ህይወቷ ይተርፋል:: ሳትፈልግ የተፈጠረው ሽል ግን እንደርሷ በህይወት የመኖር እድል አልገጠመውም:: ተመርዞ ይጨነግፋል::

የሰናይት ጽንስ ዝም ብሎ ተራ ጽንስ አይደለም:: የአብዮቱ (የሶሻሊዝም) ምሳሌ መሆኑ ነው:: ከበደ ጋሪ ቀንደኛ አብዮተኛ፣ ከዚህም ጋር አስተሳሰበ ደካማ፣ ጨካኝና ራስ ወዳድ ሆኖ ነው የቀረበው:: ስለዚህ ውጥኑ ከነራሱ መጥፋት ያለበት ይመስላል:: እናም ሆነ::

ሰናይት የሞት የሽረት ትግል ላይ በነበረችበት ጊዜ በራሷ የምትተማመነው ቅድስት ደግሞ ከምትወደው የጦር ግንባር ጀግና የጸነሰቻትን ሴት ልጅ ተገላግላ ነበር::

ስለዚህ ጽንሶች ሁሉ ተምሳሌቶች ናቸው በአብዛኛው:: ማርታን መውሰድ ይቻላል:: የማርታ የጨነገፈ ጽንስ የማንነት ጥያቄው አወዛጋቢ የሆነ የቅናትና የስሜታዊነት ውጤት በመሆኑ በዚያው ይጠፋል::

የሰናይት ጽንስም እንዲሁ ለበቀል ሲባል በተፈጠረ ግንኙነት የመጣ ስለሆነ በወዲህም የአብዮተኛውን የከበደ ጋሪንና እርሱ የሚወክለውን ርእዮተ አለም የሚወክል በመሆኑ ይጨነግፋል:: በብዙ መስዋትነት የተፈጠሩት የፋናዬና የቅድስት ጽንሶች ደግሞ የሚወክሉት የተማሩትን፣ በመፈቃቀድ እና በይሁንታ በተወጠነ ግንኙነት የተጎዳኙትን ዘመነኛ ትውልድ በመሆኑ ሲወለዱ ባናይም መጸነሳቸውን እናውቃለን::

ከጽንሰት ቀጥሎ የምናየው ጉዳይ ስለተወለዱ ህጻናት ነው:: ህጻናት በየልቦለዶቹ ውስጥ በየአጋጣሚው ይፈጠራሉ:: የአስካለ ልጅ ወርቅነህ፣ የአረጋሽ ልጅ ዮሐንስ፣ የማርታና የጌታሁን ልጆች፣ የሽታዬ ልጆች ከቤተሰባዊ ተቋም የተገኙ ወይም በነጠላ ቤተሰብ ኃላፊነት ሥር የሚተዳደሩ ናቸው:: ከእነዚሁ ጋር ደግሞ አዳዲስ የሚጸነሱ ልጆች አሉ:: የማርታ መጸነስ፣ የፋናዬ መጸነስ፣ የሰናይት መጸነስ፣ የቅድስት መጸነስ:: የሁሉም ሴቶች ጽንስ ተምሳሌትነት አላቸው ብለናል::

በሌላ በኩል አመጣጣቸውን፣ ስረ መሰረታቸውን የማናውቃቸውን በርካታ ህጻናት ገጸባህርያት በድርሰቶቹ ውስጥ እናያለን:: ከብዛታቸው የተነሳ በአካል ሳይገለጽልን የማንነቱን ሳናውቅ የምንቀረው የህጻን ልጅ ፎቶግራፍ በፋናዬ ቤት ውስጥ መቀመጡ ይነገረናል (ቋሳ ገጽ 176)::

የወ/ሮ ሺማጫሽ አገላለጽና የወ/ሮ ፋኖሴ የማንነት ጥያቄ ላይ ትኩረት መስጠት በአዲሶች ትውልዶች እየተናጋ ይስተዋላል:: የደሃ ልጅነት በጋብቻ አለመመጣጠንን ሊፈጥር ይችላል ከተባለ (በወ/ሮ ሺማጥሽ አቋም)ነው ከተባለ፣ የትውልድ ሀረግ፣ ዘር ማንዘር ማንነት መታወቅ ለጋብቻ መስፈርት ነው ከተባለ (በወ/ሮ ፋኖሴ እምነት) የዘር ሃረግን የማያውቅ ብትን ትውልድ በበዛበት የጋብቻ እጣ ፋንታ ምን ሊሆን እንደሚችል በልቦለዶቹ ውስጥ ተንጥልጥሎ የቀረ ጥያቄ ነው የሆነው::

ዶጮ እናቱን ከነህጻን ልጅ እዝሏ የጥይት ሰለባ ሆና ያጣታል፡፡ ደሳለኝ ያስጠጋዋል፡፡ ከላይ ከታች፣ ከግራ ከቀኝ ዘመድ የሌለው ነው ዶጮ፡፡ የዶጮ ለታሪኩ ያለው አስተዋጽኦ በገጸባህርይነት የተሰጠውን ስፍራ ያህል ወሳኝ አይደለም፡፡ ነገር ግን በየምእራፉ ለተገለጹት ህጻናት ቁጥር ይጨምራል፡፡

አሰለፈች በዳኜ መኩሪያን እንድትጠራላት የላከቻት ህጻን የማን ልጅ እንደሆነችና ለምን ከአሰለፈች ጋር ልትኖር እንደበቃች የተሰጠ ፍንጭ የለም፡፡ ብቻ መኩሪያ በአስቸኳይ ወደተጠራበት ወደማያውቀው ቤት ሄዶ ያልጠበቀውን የዱላ ውርጅብኝ እንዲቀበል መልእክተኛ ሆናለች፡፡ ለዚህም ነው በገጸባህርያትነት በቀረቡት ወንዶችና ሴቶች መካከል በሚታይ ግንኙነት ሳቢያ ከሚፈጠሩት ህጻናት ጋር ሌሎችም መነሻና መድረሻቸው የማይታወቅ ህጻናት በብዛት ተሰግስገው ይገኛሉ ያልኩት፡፡

አዛዥነት የኢኮኖሚ ባለቤትነት ለወንዶች የተሰጠ ሚና ነው፣ ማርገዝና መውለድ ለወንድ ታዛዥ መሆን ለሴቶች የተሰጠ ድርሻ ነው እንደተባለው ሁሉ ህጻናት የተሰጣቸው ሚና አለ፡፡ መላላክ የህጻናት ሚና ነው፡፡ ኤፍሬም ለራሔል የክህደት ደብዳቤውን የላከው ለአንድ ሊስትሮ አስይዞ ነው፡፡ ግርማ ለአበራ የሰናይትን እውነት የሚገልጽ ደብዳቤ የሚልከው በአንድ ልጅ ነው፡፡ ስምየለሽ ልጆች፣ መሰረታቸው የማይታወቅ ልጆች በተግባር ተሰልፈው ይገኛሉ፡፡

ስለህጻናት ከተነሳ ለቤተሰብ መፍረስም መነሾዎች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ጌታሁን ከሚያከብራት ሚስቱ ከማርታ የሚለያየው አባታቸው በቅርብ የሌለውን የሽታዬን ልጆች ሲንከባከብ በፍቅር ግንኙነት ተተርጉሞበት ነው፡፡

*ነጠላ እናትነት*

በሶስቱም ልቦለዶች ወንድና ሴት በተፈጥሮ ህግ በመፈቃቀድ ጥላ ሥር ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ፡፡ ሴቶች ያገቡትም ያላገቡትም የእናትነት ሚናቸውን ሲወጡ፣ ያገቡትም ያላገቡትም በወንዶች እግር ስር ሲልመሰመሱ ነው የሚታዩት፡፡ ብዙዎቹም በነጠላ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ሲንከላወሱ ይታያሉ፡፡

ወ/ሮ ሙሉን ብናይ (ቋሳ)፣ አረጋሽን ብናይ (አንጉዝ)፣ ሽታዬን እና ወ/ሮ ጠጄን ብናይ (ቢስ ራሔል)፣ ሁሉም ብቻቸውን ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ይታያሉ፡፡ ወ/ሮ ጠጄ ልጆቻቸውን በማስተማራቸው ልጃቸው ራሔል የተለየ የአስተውሎት ፀጋ የተላበሰች መሆኗ ለህይወታቸው መለወጥ መንስኤ ትሆናለች፡፡ ወ/ሮ ሙሉም አያት ከመሆናቸው በስተቀር ከወ/ሮ ጠጄ ይመሳሰላሉ፡፡ ሽታዬ ግን በራሷ የምትተማመን በሙያዋ ጸንታ ለበለጠ እድገት የምታትር ናት፡፡ በጦር ግንባር የሚዋጋ ጀግና ባሏን ተልእኮ እያሰበች የምትጽናና፡፡ አረጋሽም አንድዬውን ልጇን ዮሐንስን ታሳድጋለች፡፡ ከሽታዬ ስትነጻጸር የራሷ ደረጃ አላት በእርግጥ፡፡ ልዩነታቸው ግን አረጋሽ የሽታዬን ያህል የትምህርት ደረጃ ስለሌላት ለልጇ አለኝታነት የጓደኛዋን የሰናይትን ስውር ክንድ ትመረኮዛለች፡፡

ነጠላ እናትነት ራስን በመሰዋት ይገለጻል፡፡ ፋናዬን ብንወስድ፣ ቅድስትን ብንወስድ ለዚህ አብነት ናቸው፡፡ ፋናዬ ለየት ትላለች፡፡ ከላይ በእናቷ አጓጉል ወግ የተነሳ፣ ከወንድሟና ከአባቷ ጋር ለከፋ ህይወት የተዳረገች ነች፡፡ የፋናዬ ተሞክሮ ለየት የሚለው እናትነት ሁልጊዜ በሩህሩህነትና በደግነት የተቃኘ አለመሆኑን፣ የእናቷን ጨካኝነት አንስታ የተረከችበት ሁኔታ ነው፡፡ የእናትን ጨካኝነትና ክፋት በይፋ በመናገር እስከዛሬ ከተለመዱት በብዛት ማለት ነው በተለየ የቀረበች፣ በተቃራኒው ደግሞ ተገዳ ለወለደቻቸው ነገር ግን በአጭር ለተቀጩ መንታ ልጆቿ ራሷን መስዋእት ያደረገች፣ በኋላም የቆሰለ ህሊናዋን

በሙኩሪያ ለማገገም ስትሞክር እርሱንም ያጣች አሳዛኝ ነፍስ ጡር ሴት ናት፡፡ ግን በልቦለዶቹ ከተሳሉት ሴቶች መካከል ጠንካራና በራስ መተማመን ካላቸው ዋነኛዋ ናት፡፡

ነጠላ እናትነት አንድም ወደውና ፈቅደው የሚገቡበት (ቅድስትን መውሰድ ይቻላል)፣ አለያም ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ከጥንዳቸው በመለየት የሚመጣ (ፋናዬን እና አረጋሽን መውሰድ ይቻላል) ወይም ደግሞ ሳይፈቅዱና ሳይቀበሉት በጉልበት የሚፈጠር ነው (አሁንም የፋናዬን የቀድሞ ማንነት ማየት ይቻላል) የሴቶች አጋጣሚ ነው፡፡ ይኸኛው አጋጣሚ አስፈሪ ሆኖ የተጠቀሰበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ አያት ወ/ሮ ሙሉን ማንሳት ይቻላል፡፡

እናትነት ከልጅ አልፎ ለልጅ ልጅም ሲተርፍ ይታያል፡፡ ወ/ሮ ሙሉ ፍሬመውደድን (ወዴን) አሳድገዋል፡፡ የአፍላ እድሜን አደገኛነት ለልጅ ልጃቸው በማስተማር ራሷን እንድትጠብቅላቸው ሲማጸኗት እናነባለን፡፡

> ውድዬ ሌላ ሞት፣ ሁለተኛ ሞት፣ ከመሞቴ በፊት የምነግርሽ አለኝ፡፡ ልብ ብለሽ ስሚኝ፣ ለብዙ ያሰብኩዋት ብዙ የተማምንኩባት ልጄ፣ ተጫውታ ሳትጠግብ አምራ ሳያልፍላት፣ ሠርታ ሳትደክም፣ አልጋ ተቆራኝታ፣ ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ ሆና የምትገኘው በልጅነቷ በየዋህነትዋ ተጠግቶ፣ እወድሻለሁ ብሎ ያታለላት ወንድ በፈጠረባት ችግር አርግዛ በድብቅ አስወርዳለሁ ብላ ስራ ስሩን ጠጥታ ውሎ አድሮ በደረሰባት የአእምሮ መቃወስ ምክንያት ነው፡፡ ውድዬ በሷ ሞቻለሁ፡፡ እሷም ሞታለች፣ አለችኝ ብዬ ለመናገር አልደፍርም፡፡ እንደገና ደግሞ ሌላ ሞት ለመቀበል አልችልም፡፡ . ..
>
> . . . ከዚህ የድህነት ኑሮ ተምረሽ የረባ ሥራ ይዘሽ ታወጪኛለሽ፣ ለእህትሽ ያለሻት ተስፋ አንቺ ነሽ ብዬ ስለማምን ውድዬ ተጠንቀቀሽ ለወግ ድረሽልኝ፡፡ (ቃሳ፣ 70 እና 71)

ወ/ሮ ሙሉ ስለውርጃ ክፋትና ስለልደት ያላቸው ያሳለፉት ልምድ እንዲፈሩ አድርጓቸዋል፡፡ ጥሩ የሥነተዋልዶ መምህርት ናቸው፡፡ በግልጽ እንደእናቷ ለምታያቸው ታዳጊ ወጣት ሲያስተምሩ ይገኛሉ፡፡ በርግጥ ለውዴ ይህን ታሪክ የሚነግሯት «እህቷ» በምን ምክንያት እንደዚያ እንደሆነች እውነተኛውን ምክንያት አለማወቋ ረድቷቸው ነው፡፡ እናም አሰሪዋ ውብሸት ለአውዳመት የሰጣትን ሃያ ብር ስትሰጣቸው በገንዘብ እየደለለ ጠልፎ ሊጥላት ነው ብለው በመስጋት ነው ይህን የሚነግሯት፡፡ እናም በአያቷ ምክር ውብሸት ቤት በተመላላሽ መሥራቷን ታቆማለች፡፡ ውዴ መኩሪያ እስከሚነግራት ድረስ ምንተስኖት እናቷ መሆኗን አታውቅም፡፡

ልጃቸውን በመምከር ከወ/ሮ ሙሉ የሚመሳሰሉት የሰናይት አባት አቶ ብሩ ናቸው፡፡ ከምክራቸው በስተጀርባ ባለው አመለካከት ግን ይለያሉ፡፡ ልዩነታቸው ጾታቸውንና ያላቸውን ማህበረሰባዊ ሥፍራና በዚያም ሥፍራቸው በተሰጣቸው አቅም ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

> . . . ምሳ ለማቅረብ አስቀድማ የጣት ውሃ ስታንቆረቁርላቸው ዝቅ ባለ ድምጽ «ወረቀቱን አይቼዋለሁ፡፡ .. ይኼ ባለጌ ልጅ አብሮ ማደጉን ወንድምነቱን ረስቶታል፡፡ እሱን ግዴለም. . . አንቺ ግን የኔ ልጅ ጨዋ ነሽ . . . ለእንዲህ አይነቱ ወስላታ ፊት እንዳትሰጪ፣ ትምህርትሽን ጠንክረሽ ተከታተይ ክብርሽንም ጠብቂ . . . የብሩ ልጅ እንዲህ ናት ተብሎ ስሜም ስምሽም አጓጉል እንዳይነሳ . . . እሺ?» አሏት

ምክራቸውን እንደቃል ኪዳን መቀበሏን ለመስማት መልሷን እየጠበቁ። (አንጉዝ ገጽ 21)

በሁለቱ አዛውንት ገጸባህርያት የምክር አገልግሎት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ። አቶ ብሩ ለስማቸው፣ ለዝናቸው እንጅ ከልጃቸው የሚሹት ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ አለመኖሩን ስንረዳ፣ የወ/ሮ ሙሉ ግን በልጃቸው ማደግ የራሳቸውና የህመምተኛ ልጃቸውን ፈውስ ነው የሚሹት። ሁለቱም ተመካሪዎች ግን የተሰጣቸውን ምክር ሲያደምጡ፣ በምክሩም መሠረት ህይወታቸውን ሲመሩ እናነባለን።

ሰናይት የቤተሰቦቿን ደም መለሰች። በልማዱ፣ በባህላዊ ወጉ ደመላሽ የሚባለው ወንድ ልጅ ሲሆን ፀሐይ ግን የሴት ጀግና፣ የሴት ደመላሽ ፈጥራ አሳይታለች። ሙያዋን በልቧ የሰነቀችው ሰናይት ይፈራ የነበረውን ከበደ ዋሚን ከነ ግብረ አበሩ ገንድሳ ትጥላለች።

የወ/ሮ ሙሉ ግን እቅዱ ምኞታቸው ገና ተግባራዊ ሆኖ ባናየውም በመንገድ ላይ ነው። ውዴ ገና እያደገች ነው። ዩኒቨርሲቲ ገብታለች። የረባ ሥራ ለመያዝ እየተሰናዳችላቸው ነው። ልቦለዱ በተጻፈበት መቼት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ምሩቅ ሆኖ ሥራ አጥነት አይታሰብም ነበር። ስለሆነም 12ኛ ክፍልን ጨርሰው በስራ እጦት የተንገላቱት ራሔልና ቀለሚ እንዲሁም እነወርቅነህ የደረሰባቸው እጣ እንደማይደርስባት እንገምታለን።

አንዲትም ሴት ለውርጃ ስትንቀሳቀስ አትታይም። ማርታም ብትሆን በሀሳብ ደረጃ ታነሳውና ጊዜው ያለፈና የዳበረ በመሆኑ ትተወዋለች። ሠናይት ደግሞ የዚያ አይነቱ ሀሳቡም የላትም። በልቦለዱ ባይጠቀስም ባለትዳር የሆነች ሴት ያለባሏ ፈቃድ ብቻዋን ጽንሷን ማቋረጥ የማትችልበት ዘመን ስለሆነ ወደዚያ አለመሄዷን አንባብያን ያለንን ዳራዊ እውቀት ተጠቅመን መልሱን እራሳችን እንሰጣለን። ማርታ ግን ህጋዊ ጋብቻ ስላልፈጸመች ብቻዋን መወሰን ብትችልም ጽንሱ ከአራት ወር በላይ ስለሆነው ይቀራል።

ከልደትና ጽንሰት በተጓዳኝ መሃንነትም የሴቶች ተፈጥሮና እኩይ አጋጣሚ ሆኖ ነው የሚነሳው። መሃንነት በታየች አባጨፍቅ እና በአሰገደች ህይወት ይታያል። አሰገደች በዚህ አጋጣሚ የተነሳ ትዳሯን ፈትታ ኮማሪት መሆኗን ይነገረናል። ይህ አጋጣሚ ነው በራሔል ላይ ያለእድሜዋ ዝቅ ብላ በቅናት የጠለሸ ስም ስትለጥፍባት የኖረችው። ሌላው ቀርቶ ወ/ሮ ጠጂ እጃቸውን ለመጎዳት የሚበቁት ወንድማቸው ሚስቱ መሃን በመሆኑዋ ልጅ ለመውለድ ሌላ ሴት ዘንድ ሲሄድ እርሷ ደግሞ አጠገቧ የነበረውን ገበሬ ለማማገጥ ሞክራ እምቢ ሲላት ዮሴፍን አደረገችው ወ/ሮ ጠጂ እንደሚተርኩት። ባሏ ሚስቱን ደፍረሃል ብሎ አስሮ አሰቃይቶታል ገበሬውን። ወ/ሮ ጠጂ እርሱን ሲያስጥሉ ነው በሽጉጥ ጣቶቻቸው የተጎዱት። የጣቶቻቸው መጎዳትና ዘወትር በመሐረም መሸፈን ነው በስጋ ደዌ ሰለባነት እንዲታሙ ያደረጋቸው።

**ሴቶች ምን ያህል በራሳቸው ለመወሰን ይችላሉ?**

በራሳቸው መንገድ ነጻና በራሳቸው ውሳኔ ትዳር የሚይዙት ሴቶች ከቤተሰቦቻቸው ይቆራረጣሉ። አለበለዚያም ደግሞ በወዳጅነት ስም በቀረቧቸው ሰዎች ውሳኔና ተጽእኖ ሥር ይውላሉ። ለምሳሌ ደሳለኝ ለጉዳት ይዳረጋል። ደሳለኝ ከነጉዳተኛ ነቱ ለሽታዬ ይታጫል። ለዚህ ደግሞ የእርሷ ፍቃደኝነቷ ሳይሆን የእርሱ ሩህሩህነት ለልጆቿ ያለው አቀራረብ ልጆቿ ለእርሱ ያላቸው ፍቅር ነው። የጦርሜዳው ባሏ በህይወት እያለ የመኩሪያ

እርዳታ እንዳልተለያት ሁሉ ጀግናው ባሏ ሲሞት ደግሞ ደሳለኝን ለልጆቿ አለኝታነት ሲዘጋጅነ በባልነት ሲታጭላት እናነባለን:: ይህ ሁኔታ የሽታዬን ጠንካራ ሴትነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባና ብቻዋን መኖር የማትችል ሊያስመስላት በቅቷል:: የእርስ በርስ ጦርነቱ ሽታዬንና ቅድስትን ልጆቻቸውን ለብቻ እንዲያሳድጉ ፈርዶባቸዋል:: መነንንና ደላላው ወርቁን ደግሞ አከልደጉዳተኞች ሆነው ተደብቀው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል::

ይህ የሚያመለክተው ሴቶች የቤተሰብም ሆነ የባህላዊ አቋሞች መገለጫ እንጂ በራሳቸው ለራሳቸው ለመወሰን እንደማይችሉ ነው:: ለምሳሌ ማርታ እና ሽታዬ (*ቢስ ራሔል ገጽ147*):: ሽታዬ በመኪና አደጋ ምክንያት ተጎድታ ሆስፒታል በተኛች ጊዜ እንኩዋን ከዘመዶቿ አንዳቸውም አልጠየቁዋትም:: የማርታም እናት በስንት መከራ ከለያዩዋት ከጌታሁን መታረቋን ሲረዱ የተኛችበት ሆስፒታል ውስጥ አይንሽ ላፈር ብለዋት ይሄዳሉ:: የመቁረጣቸው ብዛት ከሆስፒታል የወጣውን አስከሬኗን እቤታቸው ለማስገባት በቁስ በመነኩሴ ተለምነው መሆኑን ስናነብ ግብዝነታቸው፣ ለፍቅርና ለእናትነት ሳይሆን ለወግ መገዛታቸውን እንረዳለን:: ልክ እንደፋናዬ እናት ናቸው::

ቤተሰባዊ ተቋምን ከሚበትኑትና ከሚያናጉት መካከል የወንዶች ክህደትና ጦርነቱ ዋነኛ መክንያቶች ሆነው ቀርበዋል:: ይህ ነጥብ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ጎልቶ ተንጸባርቋል:: ፖለቲክ፣ ባህል፣ የወንድ ትምክህተኝነት የቤተሰብን ተቋማዊነት ጥያቄ ውስጥ እየከተቱት ነው::

ሁሉም ሴቶች በአንድ ወይም ከዚያ በተለየ ሌላ ምክንያት የማህበረሰቡ አጉል ገጽታ ሰለባዎችና የማህበረሰቡ ጭለማ ገጽታ የሚንጸባረቅባቸው ናቸው:: ከከፋ ሴትኛ አዳሪነት፣ ሻል ሲል ደግሞ የአስተሳሰብና የኢኮኖሚ ጥገኝነት ይታይባቸዋል:: በአንጻራዊ ነጻና በራሳቸው የሚተማመኑት ሴቶች አንድም የተማሩት፣ አለበለዚያም በሴትኛ አዳሪነትና በኮማሪነት የሚኖሩት ናቸው:: አንድም ተምሮ ከፍያለ ደረጃ መያዝ አለያም ሁሉንም ትቶ በሴትኛ አዳሪነት ማመጽ የሴቶች ጉልበት ሆኖ ነው የሚታየው::

የመጀመሪያዎቹን ብናይ ፋናዬ በራሷ ዓለም ውስጥ በቀል ቋጥራ እንደልቧ የምትኖር ሴት ናት:: ሽታዬ የጦር መኮንን በማግባቷ ምክንያት ቤተሰቦቿ ቢያገልሏትም የእራሷ መንገድ ትክክል መሆኑን አምና እንዲያውም በአሉባልታ የፈረሰውን የጌታሁንን ትዳር መልሳ ለመጠገን የሞከረች ናት፣ ተሳክቶላት ውጤት ባያመጣም:: ቅድስትም እንዲሁ በድፍረት የመረጠቻውን ሙያ ሥነጽሁፍንና ጋዜጠኝነትን ሙጥኝ ብላ ነገር ግን የተፈጥሮ ግዳጅ የሆነውን ዘርን መተካት ከመረጠችውና ለልቦለዷ በዋና ገጸባህርይት ከመረጠችው የጦር መኮንን ትጸንሳለች::

በሁለተኛው ወገን ከፈረጅናቸው ደግሞ በሰልፉ ውስጥ ያሉት ደፋሮችና ጥቅምን የሚያስቀድሙ፣ ራስወዳዶች ናቸው:: በኮማሪነት የተሰለፉ ሴቶች ደግሞ ቢወልዱም ባይወልዱም ፍቅር አልባ፣ ገንዘብ አምላኪዎች ናቸው:: ታየች አባጨፍቅን ከ<u>ቋሳ</u>፣ አሰገደችንና ዘመናይን ከ<u>አንጉዝ</u> እነዚህ ለሁለተኛው ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለቀዳሚው ነጥብ ደግሞ ወ/ሮ ሺማጫሽን ከቢስ ራሔል ምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: ገንዘብ ብቻ የሰው ልጅ ግብ ሊሆን እንደሚገባው የሚሰብኩ ራስ ወዳዶች ናቸው:: ለምሳሌ ታየች አባጨፍቅ የልጅነት ጋብቻ ላስከተለባት ችግር ሰለባ ሆና በውርጃ ሰበብ ለመሃንነት የተዳረገች ናት:: ነገር ግን ከማንም ይልቅ መልከመልካም ሴት በሴትነቷ ተጠቅማ ሀብታም መሆን ትችላለች ብላ የምትሰብክና ለዚህ ዓላማም የምትጓዝ ናት:: ለምሳሌ ውዴን ስታባብላት እናያታለን:: ወ/ሮ ሺማጫሽ

(*ቢስራሔል*) ልጃቸውን ማርታን ከመነሻው ያልወደዱትን ደሃውን ጌታሁንን እንድትፈታ ሲያግባቡ መደለያ የሚያቀርቡላት ቡና ቤታቸውን ነው፡፡

በአስተሳሰብ ያልበሰሉት ሴቶች እርስ በርስ ሲመቀኛኙ፣ ሲጠላለፉ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ዘመናይ የአረጋሽን የጸጉር ቤቱን አልሸጥም ስትላት መርዝ በተላሰ ቅራሪ ልትገድላት ስትሞክር ተምራ እራሷን በደበቀችው መነን አመካይነት ከጥፋት ትድናለች፡፡ ቢስ ራሔል ውስጥ እነራሔል ከሞት የሚተርፉት በአሰገደችና በቀለሟ ተንኮል ሳቢያ የተመረዘው የሰርግ ድግስ በደሳለኝ መስዋእትነት ምሥጢሩ በመታወቁ ነው፡፡ የምቀኝነትና የቅናት ውጤቱ ለማጥፋት መዳረግ ነው፡፡ ስለዚህ በልቦለዶቹ ውስጥ ቅናት፣ ክህደት እነዚህ ሁለቱ ገጸባህርያቱን ለበቀል የሚያነሳሱ ነጥቦች ናቸው፡፡

ለእነዚህ አይነቶቹ ሴቶች ቅናት ባህርያቸው ቢሆንም ከዚህ አልፍ ብሎ ውጤቱን የምናየው ግን ሁለቱም ከፍተኛ በሆነ ህመም መሰቃየታቸው ነው፡፡

ልቦለዶቹ ውስጥ ፖለቲካዊ ጭብጦችንም እናገኛለን፡፡ መቼታቸው እንደሚነግርን የደርግ ሥርዓትና የነበረው የእርስ በርስጦርነት ብዙ ኢኮኖሚያዊ ድቀት እንዳስከተለ ነው፡፡ የትምህርቱ ሥርአትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባለመኖራቸው በርካታ ወጣቶች ለአልባሌ ህይወት ተዳርገዋል፡፡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ባለመደራጀታቸው በርካታ ድሆች ለእንግልት ተዳርገዋል፡፡ ለምሳሌ በየሆስፒታሉ ያለው የዝምድና አሰራር፣ በዳቦ ወረፋ መደባደብ ለጋዝ ወረፋ ሲሄዱ ማደር የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የችግሮች ሁሉ ጨንገር የሚለመጥጣቸው ሴቶችንና ህጻናትን ነው፡፡

ከዚህ መኻል አሳማኝ ያልሆኑ ትርክቶች ለምሳሌ ምንተስኖት ለምን በሽተኛ እንደሆነች አሳማኝ ነገር የለም፡፡ በክህደቱ ሳቢያ ከሆነ ልጇ አድጋ ሰባት አመት እስከሚሆናት ድረስ ጤነኛ እንደነበረች ጥቁምታ ተሰጥቶናል፡፡ ለምሳሌ መኩሪያ ለውዴ በብስጭት እንደታመመች ይነግራታል (*ቃሳ*፣ 214 - 215)፡፡ በሌላ ስፍራ ደግሞ ምንተስኖት ከ12 አመት ህመም በኋላ ስትድን ውዴ 19 *አመቷ* እንደሆነ ይነገረናል፡፡ ስለዚህ ውዴ እናቷን አለማወቋ ግርታን ይፈጥራል (147)፡፡ ጤናማ የሆኑ የሰባት አመት ልጆች የማስታወስና አከባቢን ለማወቅ ይችላሉና፡፡

ሌላው ቀርቶ ምንተስኖት የተማረች ነች እየተባልን ((154) እና ከተጠቀሰው የእድሜ ልዩነት አንጻር ምንተስኖት መማሯ ምንም እንዳልጠቀማት ይታያል፡፡ በመሆኑም ደካማና መወሰን የማትችል ገጸባህርይ ትሆንብናለች፡፡ ከልጅ መውለድ ጋር በተያያዘ ብቻ ህሊናዋ ሲጎዳ አእምሮዋ ከጥቅም ውጪ ሲሆንና ሽባ ስትሆን ለማየት በቂ ምክንያት እናጣበታለን፡፡

የፋናዬ ሰዓሊ መሆን ምንጩም ለታሪኩ ያለውም ፋይዳ በግልጽ አይታይም፡፡ (104) መኩሪያ እቤቷ ሲጋበዝ የተመለከተው ነገር ቢኖር የተወጠረ ሸራና የቀለም ብሩሾችን ነው፡፡ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ አለመጠቀሱም ሆነ በዚያች ቅጽበት ብቻ መጠቀሱ ለታሪኩ የሚሰጠው ጥቅም የለም፡፡

## ሴቶች ችግራቸውን የሚቋቋሙት እንዴት ነው?

ሴቶቹ የተማሩትም ያልተማሩትም ሁሉም ከችግር ጋር እየተጋፉ የሚኖሩ ናቸው፡፡ የገንዘብ ችግር፣ ተቀባይነት ያለማግኘት ችግር፣ ፖለቲካዊ ችግር ሁሉም እያገላበጡ የሚገርፏቸው ሴቶች ገጸባህርያት አሉ፡፡ ያላቸው ሀብትና ጉልበት የመልክና ቁመናቸው ማራኪ መሆን፣ ጥሩ ምኞት፣ እና ለእናትነት ብቁ

መሆን ናቸው:: ከዚህ ውጪ በኢኮኖሚ ራስን መቻል ሚያጋጥሟቸውን አካባቢዊም ሆነ ቤተሰባዊ ችግሮች ለመቋቋም ሲከብዳቸው፣ ሲወድቁ ሲነሱ ይስተዋላሉ:: ነገር ግን ከዚሁ ጎን ከዚህ ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረት አለ:: ፉኮ ይህንን የመቋቋም ስልት (strategy) ይለዋል:: እነዚህ ስትራተጂዎች በሴቶቹ በራሳቸው ለሴቶቹ የተፈለሰፉ ናቸው በአብዛኛው:: ይህ አገላለጽ ከልቦለዶቹ በመነሳት የተሰነዘረ መሆኑን እዚህ ላይ መግለጽ ይኖርብኛል::

ችግሮቻቸውን ሁሉ በምን ሁኔታ ነው የሚጋፈጡት? ያልን እንደሆነ የጠበቀ ጓደኝነት እና ምስጢረኛነት፣ የቡና ጠጡ ወንፈልና ማህበር፣ በችግር ጊዜ የቤተሰብ ድጋፍን ማግኘት፣ እና በመማር ነው::

**ቡና ጠጡ**

የቡና አፈላል ሥርዓትና ገለጻ በሶስቱም ልቦለዶች እጅግ የበረከተ ነው:: በየገጸባህርያቱ ግንኙነት ምእራፍ ቡና ሲገባበዙ እናገኛቸዋለን:: ቡና ጠጡ ማለት በዚህ አገባብ በቤት ውስጥ ተሰናድቶ ከሁነኛ እንግዳ ወይም ከጎረቤት ጋር ተጠራርተው በመሰባሰብ ከአቦል እስከረጃ የሚፈላውን ማለት ነው:: በፀሐይ ብርዕ ባህላዊው የቡና ስርዓት ትርጉም ይዞ፣ ዓላማ ሰንቆ የሚሰናዳ ሆኖ እናገኘዋለን:: ቋሳ ውስጥ ወ/ሮ ሙሉ ከጎረቤቶቻቸው የሚቀራረቡት በልጃቸው በፍሬመውደድ ሳይቀር በሚናፈቀው የቡና አፈላላቸው ነው:: ቡና ጠጡ ሴቶቹ እርስ በርስ የሚወያዩበት፣ ውሏቸውን የሚቃኙበት፣ ችግራቸውን እያነሱ የሚጥሉበት፣ ለችግሮቻቸው መፍትሔ የሚሹበት ነው::

<u>አንጉዝ</u> ውስጥ በአበይትነት የተተኮረባቸው ሴቶቹ ሁሌም ሲያወጉ፣ ምሥረጢርና ጉዳዮቻቸውን ሲያነሱ ሲጥሉ፣ ደስታና የምስራች ሲለዋወጡ፣ የሚታዩት በቡና ጠጡ ጊዜ ነው:: ሌላ ጊዜማ ባተሌ ናቸው:: ቡና መጠጣት ከድካምም አረፍ መባያ ነው:: ለምሳሌ ምንትዋብ የጠላ እቃዎቿን ታጥብ እንደሆነ፣ አሻሮ ታገላብጥ እንደሆን አቋርጣ ትመጣለች፣ ቡና ጠጡ ሲባል:: ጸብም የሚረግበው ቡና ሲፈላ ነው:: ለምሳሌ የመነንና የአረጋሽ የከረረ ጸብ የሚሰክነው ቡናው ተፈልቶ ጎረቤት ተጠርቶ ጨዋታው ሲደራ ነው:: ጠላትና ወዳጅም የሚለየው እዚያው ነው:: ዘበናይ የላከችው ጠላ መርዝ የተቀየጠበት መሆኑን የሚያረጋግጡት በቡና ጠጡ ላይ ነው::

ቡና አንዳንዴ የሴቶቹ ብቻ ሳይሆን የወንዶቹም ህሊና የሚሰክንበት ነው:: ቁም ነገር የሚወጋበት ነው:: የወ/ሮ ሙሉ ወዳጅ አብዬ ቅጣው ሲመጡ ጎረቤቱ ሁሉ የአርበኝነት ውሏቸውን ታሪክ ለመስማት አንድ ጊዜ ከተሰበሰቡ ቤቱን ለመልቀቅ ጊዜ ይወስድባቸዋል::

ጌታሁን ከ11 ወራት የቤት ውጪ ስደት በኋላ፣ ከማርታ ጋር ያለው ግንኙነት በፍቺ መቋጨቱ እውን መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ ቀጥታ ወደቤቱ ሄዶ ያደረገው ቡና ማስፈላት ነው:: ስሜቱ እርክት ሲል ይታወቀዋል:: በዚያውም ኑሮውን በአዲስ ለመጀመር ይወስናል:: የህሊና ተሀድሶ ያደርጋል፣ ከሚያጣጥመው ቡና ጋር:: በአንጻሩ ደግሞ የተስፋዬ ጓደኛ የነበረው ፈለቀ እቤቱ ሲኬድ ቡና የለ:: ተስፋ የሚታይበት ሕይወት የለ:: ሚስቱ የኤድስ በሽተኛ ስለሆነ ልጆቹን ይዛ ወደዘመዶቿ መሄዷን በራሱ አንደበት ሲገልጸው (<u>ቢስ ራሔል</u>፣ 341) የቤቱም መቀዝቀዝ ከዚሁ ጋር መያያዙ ይታወቃል::

መኩሪያ ለፋናዬ ያለውን ፍቅርና የጋብቻ ፍላጎት ለመግለጽ የመረጠው መንገድ በጓደኛዋ በምንተስኖት በኩል መሄድን ነው:: በእርግጥ የፋናዬና የምንተስኖት ጓደኝነት

የተመሰረተው በራሱ በመኩሪያ አማካኝነት ነው። ፋናዬን ዳሪኝ የሚለውን ቁም ነገር ለምንተስኖት የሚያጫውታት በሰከነ ድባብ ቡና አፍልታለት እየተጫወቱ ሳለ ነው (ቋሳ፣ 231)።

ስለዚህ የቡና አፈላልና ግብዣ ለቁም ነገር መወያያ የቤት ውስጥ ወይም ኢመደበኛመድረክ፣ ለድባብ መቀየሪያ ሆኖ በመታየቱ ፀሐይ ሲኒና ረኮቦትን ለዓላማ ተዘርግቶ ታሳየናለች። የሴቶች ወግ ጽኑ መድረክ ሆኖ ቀርቧል።

## ጓደኝነት

ጓደኝነት በሁሉም የፀሐይ ልቦለዶች ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ አለው። ጓደኝነት ስል በተመሳሳይ ጾታ ያሉ ሰዎች፣ ሆድ ለሆድ የሚተዋወቁበትን፣ ክፉና ደጉን አብረው የሚካፈሉበትን ነው። ህብረተሰቡ ከተመሳሳይ ጾታ ውጪ ያለውን ጓደኝነት እንደማይቀበለው በጌታሁን ህይወት እናያለን። ቢስ ራሔል ውስጥ ጌታሁን ከሽታዬ ጋር ባለው መንፈሳዊ የወዳጅነት ቅርበት ለችግሯ ተካፋይ ሊሆን ሲሞክር ነው ይህ ወዳጅነታቸው በፍቅር ግንኙነት ተተርጉሞ ለትዳሩ መፍረስ፣ ለማርታ መሳሳት ያበቃው። ይህም ብቻ አይደለም። ዱርየዎች ሲነጥቋት ያገኛትን መንገደኛ ሴት ሲያግዝ በመገኘቱ በባሏ ተደበደበ፣ ወሬው ማርታ ዘንድ ደርሶ በግጭቱ ላይ ቤንዚን ሆነ።

ማርታ በታሪኩ ምዕራፎች ለአንዴም የምትጠቀስ ጓደኛ የለቻትም። ከነአረጋሽ ከነቅድስት አንጻር ሲታይ ብቸኛ ሆና ነው የምናገኛት። ጓደኛነት በቀደሙት ልቦለዶች የልብ አውቃነት፣ አጋርነት፣ መላና የችግር መውጫ መንገድ በጋራ የሚፈለግበትና የሚገኝበትም ነበር። እናም ማርታ ጓደኛ አልባ ናት ይበልጡን ጊዜ። ለሁለተኛ ትዳርዋ ስትሰናዳ ግን ሚዜዋን ሮዛን ብቻ እናገኛታለን። እርሷ ናት ከሰርጉ ሽርጉድ መካከል የማርታን ልብ የከፈለውን ችግር ተጋርታ የማበረታቻ ምክሯን የምትለግሳት።

ዘግይታለች እንጂ ማርታ ልቧ ከፈቀደው ከቀድሞ ባሏ ለመታረቅ ስትወስን ይህ ውሳኔዋ መጥፎ ያለመሆኑን ነው የምትነግራት። የሮዛ ምክሯ ማርታን ቢያንስ የህሊና እረፍት ልታገኝበት ወደበቃችው እርቅ እንድትገሰግስ አድርጓታል።

ጓደኛ የሌላቸው ሴቶች አንድም ችግራቸው የሚባባስና ለህልፈት የሚዳረጉ (እንደማርታ) አለያም ከፖለቲካ ሰዎች የተጎዳኙ ናቸው። ሽታዬ የሴት ጓደኛ የላትም። መኮንኖችን የሚያገቡ የጓደኛ ምክር አያሻቸውም ማለት ነው። ሽታዬ ብቻዋን ነው ፍላጎቷንና ህይወቷን የምትመራው። ኑሮዋን የሚከታተሉት ቤተሰቦች ብቻ ናቸው ጣልቃ እየገቡ ችግር ለመፍጠር መሞከራቸው የሚነገረን።

ከጦር መኮንኖች መዋዋላቸው፣ ከፖለቲካ ከድሬ መሻረካቸው ከሚፈሩና ከሚከበሩ ሰዎች ጥላ ሥር የዋሉ በመሆናቸው ጓደኞቻቸው ቢሰሙ እንኳዋን ምንም አስተያየት፣ ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ አይሰጡም። ይልቁንም በጸጥታ ነው የሚያዳምጧቸው። አለበለዚያም የሚስማሙበትን የላይ የላይ እርምጃቸውን ሲቃወሙ ነው የምንመለከታቸው።

ጓደኝነት ምሥጢርን መጋራት ማለት ነው። በመሆኑም በጓደኝነት መካከል ምስጢርን አውጥቶ አለመናገር ለግጭት እንደሚዳርግ እናያለን። ለምሳሌ ሰናይት ያንን ጠንካራ የጓደኞቿን ተቃውሞ ተሰናዝራ፣ አገር ጉድ ያሰኝ ድርጊት የፈጸመችው ህብረተሰቡ ሲመኘው የነበረውን የበቀል ተግባር ለመፈፀም መሆኑን የምትገልጽላቸው ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ ነው።

ቅድስት ከኮሎኔል ጅግሳ መጸነሷንና ፍቅር መመስረቷን ለነአረጋሽ የምትነግራቸው በራሷ ሁሉን ነገር ጨርሳ ነው።

አረጋሽ ያባቷን ገዳይ ከገባቸው ከሰናይት ከተቆራረጠች በኋላ ሰናይት በምስጢር አድርጋ ትልቅ ሱቅ ትከፍትላታለች፡፡ ከበደን እንደምታገባ ለአረጋሽ ስትነግራት ሰናይት ደግማ ማብዷን ነበር የተቀበለችው፡፡ ጓደኝነት ልክ እንዳለው የምናይበት ምእራፍ አለ እዚህ ነጥብ ላይ፡፡ ሠናይት ከበደን የምታገባው ለበቀል እንደሆነ ስለምታውቅ ይህንኑ የልቧን ፍላጎት ለምትወዳቸው ጓደኞቿ አልተነፈሰችም፡፡ እነርሱም ይህን ባለማወቃቸው ነው የፊትለፊት ተግባሯን ብቻ እያዩ ጓደኝነታቸውን የቀነሱባት፣ ፊታቸውን ያዞሩባት፡፡ ስለዚህ ጓደኝነት ችግርን በጋራ መፍትሔ ማሸነፊያ የመሆኑንም ያህል በጋራ ጓደኝት ውስጥ ግላዊ ማፈንገጥም አስፈላጊ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ ማለት ነው፡፡ ተናጠላዊ ጀግንነት በድብቅነት ይገኛል፡፡

የሆነ ሆኖ የሴቶቹ የጓደኝነት ስሜት በ<u>ቢስ ራሔል</u> የቀነሰ ይመስላል፡፡ ከዚያ ይልቅ የወንዶቹ የእርስ በርስ ጓደኝነት ጠብቆ ይታያል፡፡

**የቤተሰብ ድጋፍ**

የቤተሰብ ድጋፍ ለችግር ማቃለያ ሆኗል ስንል በአበይትነት የተቀረፁት ሴት ገፀ ባህርያት ሁሌም ብቻቸውን ግባቸውን እንደማያሳኩ፣ ሲሸነፉ ገመናቸውን የሚሸፍን የራሳቸው ሰው እንደሚያሻቸው ስለሚታይ ይህንን የታሪክ አከሄድ በመመርኮዝ ነው፡፡ የምንተስኖት አጋጣሚ ለዚህ በአብነት ይጠቀሳል፡፡ ይመጣል፡፡ ምንተስኖት በልጅ ምክንያት ኑሮዋ ሲመሰቃቀል ችግሯን ቁስሏን የሚጋሩት ወ/ሮ ሙሉ እናቷ ከዚያም አልፎ አጎቷ አቶ ተገኑ ናቸው፡፡

የቤተሰብ ድጋፍን ለማግኘት ደግሞ ፍቅርና ታዛዥነት ወሳኝ የሆኑበት አጋጣሚ መኖሩን የምንረዳበት ሁኔታም አለ በትዳር ህይወቷ ውስጥ የማርታንና የቤተሰቦቿን ግንኙነት ስንመለከት (*ቢስ ራሔል*)፡፡ እሺ ማለት የሀብት ወራህ ያደርጋል እምቢታ የቤተሰብንና የዘመድን ፍቅርን እንዲሁም ንዋያዊ ብልጽግናን ያስነፍጋል፡፡

ሠናይት በከበደ ዋሚ እጇ ለጋብቻ በተጠየቀ ጊዜ ያሸሹዋት ወንድሞቿ ናቸው፡፡ ማርታ የምትወደውን ጌታሁንን እናቷና መላው ቤተሰቧ አንቀበልም ባሏት ጊዜ ፍላጎትዋን ከግብ ያደረሰችው በወንድሟ ረዳትነት ነው፡፡ ያለእርሱ ተገንነት ከጌታሁን አትጣመርም ነበር፡፡

**የሥራ ዘርፍ ምርጫ**

በዚህ ንዑስ ርእስ ሥር የሴት ገጸባህርያቱን ማንነት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የተማሩትን በአንድ ወገን፣ ያልተማሩትን ደግሞ በሌላ ወገን፡፡ ሁሉም ግን ችግርን መቋቋም የሚሞክሩት ገንዘብ የሚያገኙበትን ስራ በማፈላለግ ነው፡፡ ሴትኛ አዳሪነት ለምሳሌ፡፡ በዚህ መስክ የሚሰማሩት ያልተማሩትና ፈት ወይም ሁሉም ባይሆኑ የሙት ሚስቶች የሆኑት መሆናቸው ቀደም ሲል ተገልጧል፡፡ በዚህ ሙያ ተሰማርተው የሚገኙት ሴቶች ቀናተኞች እና ጨካኞች ናቸው ብለናል፡፡

አሰገደች ከምትቸረችረው ጠላ ጋር ለራሔል ክፋት ስትደግስ ነው የምትውለው፡፡ ዘበናይ ደግሞ የጸጉር ቤት ለማግኘ ት ስትል ሰውን በተቀመመ መርዝ ለመግደል ስትሞክር ነው የምናያት፡፡ ወ/ሮ ሺማጫሽ ለማርታ ትዳር መፍረስ ቀን ከሌሊት ግድግዳ እንደቆፈሩ ከጓደኛቸው ከወ/ሮ ደብሬ ጋር እንደዶለቱ ነው የሚውሉት፡፡ ማርታ የሚመክሯትን ምክት ብትቀበል ቡና ቤታቸውን ሊለቁላት ሀብት በሀብት ሊያደርጓት ነው ቃል የሚገቡት፡፡ ለጌታሁን ያላቸው ጥላቻ ለልጅ ልጆቻቸው እንኩዋን

ፍቅር አልሰጣቸውም፡፡ ምክንያታቸው ጌታሁን መሰረቱ ደሀ ነው የሚል ነው፡፡ ቂመኛና የጥላቻ መንፈስ ይፀናባቸዋል እነዚህን፡፡

ታየች አባጨፍቅ የሴት ልጅ ውበቷ ለሀብት መሰረት ነው ብላ ነው የምታምነው፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ማሳያዎች የምንመለከተው ግን ገንዘብ ማግኘት ብቻውን መልካም ሰብእናን እንደማያላብስ፣ ይልቁንም ለክፋትና ለእርስበርስ መጠቃቃት ሥረ መሰረት መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ አለማወቅ፣ አለመማር ለዚህ እንደሚዳርግ እናስተውላለን፡፡ የግል ችግርን ለመወጣት፣ የእለት እንጀራን ለማግኘት ቢረዳም ዘለቄታዊ ለሆነ የጋራ እድገት እንደማይበጅ ያሳያል፡፡ ጊዜያዊ መፍትሔ ነው፡፡

ራሔል ብቻ ናት በዚህ ረገድ ውጤታማ የሆነችው፡፡ ከጉልት ንግድ ጀመረች፡፡ የጽዳት ስራ ቀጠለች፣ በራሷ ምርጫ፡፡ ይህ ጎዳና ወደትልቅ ሰገነት እንደሚያወጣት አምናለች፡፡ ከዚያም እድል በጄምስ ዊሊ አማካኝነት እጇን ዘርግታ ተቀበለቻት፡፡ አየር መንገድ አስተናጋጅ ሆነች፡፡ በግል ሥራ ተነስታ ወደ ትልቁ ተቋም ወጣች፡፡ ጀምስ ዊሊ ግን ራሔል ለትዳር ዝግጁ አለመሆኗን ስትገልጽለት አገሩ ገብቶ በመሰረተው ትዳር ለኤድስ በሽተኛነት ተደርጎ ለሞት መብቃቱን በደብዳቤ አማካኝነት እንረዳለን፡፡

ሲስተር ፋናዬ ሌላዋ የተማረች ገፀባህርይ ናት፡፡ በተደረገላት በጎ አድራጎት ህክምናን መርጣ ሲሰተር ሆናለች፡፡ በኩፍኝ በሽታ የሞቱባትን ጨቅላዎቿን እያሰበች የብዙዎቹን ህይወት ለመታደግ አስባ አቅዳ ዘልቃበታለች፡፡

ራሔልና ፋናዬ በአማካኝ ደረጃ መማራቸው የሚመርጡትን እንዲያውቁ ረድቷቸዋል፡፡ ከእለት አልፎ ለዘለቄታ፣ ከራስ አልፎ ለሌሎች ማሰብ አስችሏቸዋል፡፡

### *ተደጋጋሚ ገለጻዎች እና የታሪኮቹ ሰንሰለታዊነት*

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የጸሐይ ልምዶችና ተዘውታሪ የሆኑ መደሰቻዎቿ በሦስቱም ልቦለዶቿ ውስጥ በተቀረጹ ሴት ገጸባህርያት ልምድነት ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ሥእልን መሳል፣ በልዩ የጽሞና ድባብ ውስጥ ሲሆኑ ብራንዲ መጎንጨት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህን የተማሩት ገጸባህርያት ልምድ ነው፡፡ እንደገናም ለአበባ ያላት ፍቅር ልዩ ነው፡፡ አበባ ተምሳሌታዊ አገባብ ይዞ በሦስቱም ልቦዶች ተጠቅሷል፡፡

> ከተቀመጠበት የጋለ ግንባሩን ስማ ያመጣቻቸውን አበቦች ከማስቀመጫ ውስጥ ለማድረግ አልፋው ጥግ ይዛ ወደተቀመጠችው ጠረጴዛ ተራመደች፡፡ በተለያዩ አቅጣጫዎች እያዘነበለች ከፍና ዝቅ በማድረግ በይበልጥ ዐይን እንዲስቡና ውበታቸው ይፋ እንዲታይ ጥበብ ባለው ሁኔታ አበቦቹን በማስቀመጫው ውስጥ ካስተካከለች በኋላ ውዷን ጠርታ ውሀ አስመጥታ ጨመረችበት፡፡ ማሰማመሩን ከበቃች በኋላም በፈገግታ እንደደመቀች ዞራ ብትመለከተው ከነበረበት ሳይነቃነቅ ፊቱ ጠቁሮ ተመለከተችው፡፡ ከወትሮ ሁኔታው እጅግ ተለየባት፡፡ እየጨነቃት ተገረመች (<u>ቋሳ</u>፣ 41)፡፡

በሁለተኛው ልቦለድ በ*አንጉዝ* የአበባ ታሪክ በተለየ መልኩ ነው ተገልጾ የምናገኘው፡፡ ይህም ልዩ የአቀራረብ መልክ ልዩ ትርጉም ይዟል፡፡

> .. . ፖስታውን በጥንቃቄ ከፈተችው፡፡ ያየችው ነገር ስላስደነቃት በአካባቢው ያሉ ሰዎች እስኪታዘቧት ድረስ የምርዋን ሳቀች፡፡ ያስገረማት ስጦታም የተቆነጠረ የሰባ አፈርና የአበቦች ፍርፋሪ ነበር፡፡ የላኪውን ሰው ማንነትም

> ወደ ኋላ ከልዩ ልዩ አበቦች ፍርፋሪ ውስጥ ባገኘቸው ፎቶግራፍ ተረዳች። ሊሸኛት ከተሰበሰበው ሰው መካከል እሸቱም እንደነበር አወቀች። ቃላት ሳይደርብበት የላከላትን ስጦታ በልዩነቱ አክብራ ከቦርሳዋ ውስጥ አኑራው ነበር። ጀርመን ከገባች በኋላ ትዝታና ናፍቆት ሲወዘውዛት የእሸቱን የአበቦች ፍርፋሪና የአገሯን አፈር እንደመፍትሔ ናፍቆት ታሸተው ነበርና የእሸቱን ደብዳቤ ካነበበችም በኋላ የደረቀውን አበባና የአፈሩን ጠረን ወደ ውስጧ ማገችው። እሸቱንም በአዘኔታ እንጂ በፍቅር ስሜት አላሰበችውም (<u>አንጉዝ</u>፣ 178)።

*ቢስ ራሔል* ውስጥ *ምሥራቅ*፣ ጌታሁንና ራሔል በፍቅር መተሳሰባቸውን ለማውጣጣት የተጠቀመችው አበቦችን የተሰጣጡ በማስመሰል በፈጠረችው አጋጣሚ ነው።

> «እኔ እንኩዋን የምናገረው የለኝም። እቃው ይናገር እንደሆነ አላውቅም» አለችና ይዛው ከነበረው የላስቲክ ከረጢት ውስጥ አበባዋን ከነማስቀመጫዋ አወጣቻት። ከተቀመጠችበት ተነስታ ከፊት ለፊቱ ጠረጴዛው ላይ አኖረቻት። ጌታሁንም በፈገግታና በመደነቅ አበባዋን ተመለከታት። መለስ ብሎም የምስራቅን ዐይኖች እየመረመረ
>
> «ግሩም መልእክት ነው. . . ማን ነው? የላከልኝ ሕይወትን እንዳጣጥም የመከረኝ?» አላት ረጋ ብሎ (<u>ቢስ ራሔል</u>፣ 391)።

በሌላው ጫፍ ደግሞ ራሔል ዘንድ የሆነው የሚከተለው ነው።

> «ለኔ ነው ሐኒዬ . . .?» አለቻት ባንገተ ረዥሟ የነሀስ ማስቀመጫ ውስጥ የነበረችውን አበባ ተቀብላ ራሔል አሸተተቻት።
>
> «አዎ ላንቺ ነው።» አለቻት ሐና ውስጧን እየጨነቃትና እየሳቀች።
>
> «አመሰግናለሁ ሐኒዬ። አበባዋም ማስቀመጫዋም በጣም ቆንጆ ናቸው። ሁልጊዜም በስምሽ አስቀምጥበታለሁ። በጣም አመሰግናለሁ።» አለች ራሔል በደስታ።
>
> «ስጦታው ተልኮልሽ ነው።» አለች ሐና ቀጠል አድርጋ።
>
> «ከማን?» አለች ራሔል ደንገጥ ብላ።
>
> «ጌትዬ ነው የላከልሽ . . . (<u>ቢስ ራሔል</u>፣ 392)።

በሦስቱም ልቦለዶች የአበባ አገባብ የተለያዩ ውክልና ይዞ ነው። በ<u>ቋሳ</u> ውስጥ የሚገኙት የአበባ በረከቶች ሁሉም ማለት ይቻላል የሚወክሉት መልስ ያላገኘን የአንድ ወገን ፍቅር ነው። ህሊና ያመጣችውን አበባ ውብሸት በደስታ ተቀብሎ አላደነቀውም። አሰለፈች በዳኔ የሚኩራያን ቢሮ ስታጸዳ በየጊዘው ታኖራቸው የነበሩ አበቦች ከመኩሪያ በኩል ትኩረት አላገኙም። በ<u>አንጉዝ</u> ደግሞ ጭራሽ ህይወት የሌለው ደረቅ የአበባ ፍርፋሪ ነው የምናገኘው። ይህም እንደቀደመው ሁሉ ምላሽ ያላገኘን ፍቅርን በእንጭጩ ደርቆ የቀረ ያንድ ወገን ፍላጎትን ነው የሚወክለው።

ሦስተኛው ልቦለድ ማለትም <u>ቢስ ራሔል</u> ውስጥ ግን መልእክቱ አዎንታዊ ምላሽ ያገኘ በረከት ሆኖ ነው የቀረበበው። ጌታሁንና ራሔል በደስታ ተመስጠው ነው የደረሷቸውን አበቦች መዓዛ የሚያጣጥሙት። ከላይኞቹ መጻህፍት የአበባ ተምሳሌቶች የሚለየው ግን ይህኛው ለተፈላላጊዎቹ ጉብሎች የደረሰው ህይወት የሚዘራው አበባ የተሰናዳውና የታቀደው በሶስተኛ ወገን አማካኝነት ነው። በዚህ ጽሁፍ ኋለኛ ክፍል እንደምንመለከተው ራሔልና ጌታሁን ለመጣመር የሚበቁት በሶስተኛ ወገን ግፊት በጓደኝነትና በአሳቢ ወገኖች አማከኝነት ነው። እድሜ ለምስራቅ።

መምህርነት ሌላው ተደጋግሞ የሚጠቀስ ሙያ ነው:: መምህርነት መደጋገሙ ብቻ ሳይሆን በዚህ ሙያ መሰለፍ ደፋርና በራስ መተማመን ያለበትን ስብእና እንደሚያላብስ ሆኖ ነው የቀረበው:: ለምሳሌ ሰናይት በአንጉዝ ከጅምሩ አንስታ በመምህርነት ሰልጥና ህዝብን ታገለግል የነበረች ናት:: ይህ ሁኔታ ለኋላ ሰብእናዋ ጥንከሬ መሰረት የሆናት ይመስላል:: ደመኛዋን ከበደ ጋሪን አግብታ በዚህ ሙያ ተሰማርታ ሳይሆን የሂሳብ ሰራተኛ ሆና ብናገኛትም ለዚህ መሰረቱ የቀድሞ ተሞክሮዋ ነው ማለት ይቻላል:: በእርግጥ ምንም ሙያዊ ክሂል እንዳላት ሳይነገረን በሂሳብ ያዥነት ተቀጥራ ስናገኛት እንዴት? የሚል ጥያቄ ሊያጭርብን መቻሉ አያጠያይቅም::

መምህርት በለጠች ሌላዋ ምሳሌ ናት:: መምህርቷ በፖለቲካ ሥልጣኑ አገርን ያንበረከከውንና «ሞኝም በይኝ ደፋር በጄ ውስጥ ሳላስገባሽ አልቀርም» (አንጉዝ፣ 208) ብሎ የፎከረውን ከበደ ጋሪን በድፍረት የተጋፈጠችና  ያልተረታች ሴት ናት:: በዚሁ መጽሀፍ ውስጥ ሰናይት ለኋላ ገድሏ አነሳሽ ጉልበት የሆናት ሰልጥና ተሰማርታበት የነበረው መምህርነት ነው ማለት እንችላለን::

መምህርነት ድፍረትን አላባሽና የራስ መተማመን መንስኤ ብቻ አይደለም:: በመልካም ገጸባህርያት ዘንድ ተፈላጊና ህልም ሆኖ የሚታለም ሙያ ነው:: ጌታሁን ከገንዘብ ሚኒስቴር የሂሳብ ስራ ሙያውን ወደመምህርነት የቀየረ (ቢስ ራሔል፣ 257) ከዚህም አያይዞ የፖለቲከ ፓርቲ አባልነቱን አሻፈረኝ ብሎ በድፍረት ደብተሩን ለመመለሰ  የቀረበ ነው (ቢስ ራሔል፣ 385):: መምህር ከሆነ በኋላ የትፍስህት አምባ ተግባርና ተልእኮውን ሲያሳካ እናነባለን:: ፋናዬ ህክምና ሙያ ከማጥናቷ በፊት መምህርነት ለምርጫ በህሊናዋ መጥቶ ነበር:: ሁለቱን ሞያዎች ብዙኃን ውለታ ዋይዎች መሆናቸውን ታምናለች:: የልጆቿ ኒት ወደ ህክምናው እንድታደላ አድርጓታል::

በፀሐይ ልቦለዶች ውስጥ በአእምሮ ህመም (መደንዘዝ) የሚሰቃዩና በድንገትም ከዚህ ድንዛዜ የሚነቁ ገጸባህርያት እናገኛ ለን:: ከባድ ሀዘን ለአእምሮ ህመም፣ ከባድ ደስታ ደግሞ የደነዘዘ አእምሮን ለማንቃት ሲውሉ ይታያሉ:: ከመጀመሪያው ልቦለድ ብንነሳ ዋናዋ ገጸባህርይ ምንተስኖት ለ12 አመታት የአእምሮ በሽተኛ ሆና ከኖረችበት ሁኔታ በአንድ ጊዜ  ስትነቃ እናነባለን:: ለዚህ የዳረጋት ደግሞ በእጮኝነት ሲኖሩ በማርገዟ ብቻ አላውቅሽም ብሎ ገሸሽ ከአደረጋት ከውብሸት የደረሰባት በደል መሆኑ ይነገረናል:: ከወለደችም በኋላ ልጇ ታምማ ማሳከሚያ ሲጠየቅ አላውቅም ብሎ ያደረሰባት የጭከኔ ቅጣት በሶስተኛ ወገን ይተረክልናል::

በእርግጥ የጊዜ አለመጣጣም የታሪኩን ፍሰት የሚያደነቃቅፍ ቢመስልም ምንተስኖት የማታ ማታ ለእርሷ ይወግን የነበረውን የውብሸትን ኳደኛ መኩሪያን ስታገኝ ነው ድንገት «ልጄስ» ብላ ነፍሷን የምታውቀው:: በእርግጥም አንድ ጥያቄ እዚህም ላይ ሊነሳ ይችላል:: ምንቴ የተከበረችና ስራ የነበራት፣ በአጎቷ አባባል ምሁር ተብላ የተገለጸች ሆና ሳለ አንድ ልጇን እንዴት መንከባከብ አቅቷት ለአእምሮ ህመም ለሚዳርግ ሽንፈት በቃች ልንል እንችላለን:: ይህ ሽንፈቷ ምናልባት የነጠላ እናትነት ጉዳይ አሳሳቢ ችግር መሆኑን ለማስተላለፍ የተመረጠ ሊሆን ይችላል::

የአንጉዝ ሠናይት ሌላዋ የምንተስኖት ገጠመኝ ተጋሪ ናት:: ሰናይት ከምንቴ በተሻለ ለመደንዘዟና ለመንቃቷ ምክንያት በበቂ ቀርቦላታል ማለት ይቻላል::

በመምህርነት ትሰራበት ከነበረው ገጠር አባትሽ ታመዋል ተብላ ከተጠራች በኋላ አዲስ አበባ ስትደርስ አባቷና ሁለቱ ወንድሞቿ በቀይሽብር መሞታቸው በአንድ ጊዜ ሲነገራት ራሷን ስታ ትወድቃለች:: በዚያው ቀውስ ትሆናለች:: ለአመታት የጓደኛ ዋ የአረጋሽ «እዳ» ሆና በሰባራ ባቡር አከባቢ የታወቀች እብድ እየተባለች ኖራለች:: ማሳከሙ፣ መጠበቁና መንከባከቡ በብቸኛዋ አረጋሽ ትከሻ ላይ ይወድቃል:: ጓደኝነት ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን የሚያመለክተን ግንኙነት ነው የሁለቱ ግንኙነት:: እድሜ ለጓደኛቸው ለቅድስት ከአሜሪካን መጥታ ሰናይትን ስታሳክማት ከአንድ አመት በኋላ ወደህሊናዋ ተመልሳ ሰው ትሆናለች:: ከዚያ በኋላ ኑሮን «ሀ» ብላ መኖርና የበቀል መሰናዶዋን ትጀምራለች:: መጀመሪያ ወደ ህሊና መመለስ፣ ራስን መሆን ፣ ከዚያም ራስን ማወቅ፣ በመጨረሻም ህልምን ለማሳካት መፍጨርጨር::

የምንተስኖትንና የሰናይትን ያህል ባይሆንም በ<u>ቢስ ራሄል</u> ተመሳሳይ የአእምሮ መደንዘዝ እጣ የገጠመውንና በመውደቅ ምክንያት ጭንቅላቱ በድንጋይ እወደቀበት ሲመታ የደነዘዘው ካቻ ገሞራው (መሞቱ በቤተሰቦቹ የሚታመነው ግርማ ወልደኪዳን) አእምሮው ሲመለስ እናነባለን:: ከዚያም ለአመታት እንደወፈፌ ሲቆጠር ከኖረበት ከአዶላ ወርቅ ማእድን ስፍራ ተነስቶ ወደ አገሩ ይመለሳል::

እነዚህና ሌሎች እዚህ ያልተጠቀሱ ገለጻዎችና የታሪክ አጽቆች በሦስቱም ልቦለዶች ውስጥ ለጭብጥ ማዳበሪያነት እና ለታሪክ ማራመጃነት መገልገላቸውን ማስተዋል ይቻላል::

**ሴትነት በወንድ ገጸባህርያት ሲገለጽ**

የበላይነት ምንጊዜም የወንዶች ሆኖ እናገኘዋለን:: በጉልበትነ በውሳኔ ሰጪነት በሥራ ቁንጮነት ያሉት እርሱ ናቸው:: ይህንንም የበላይነታቸውን ማሳየት የሚችሉት በሴቶች ላይ ነው:: ሥራ ለማስቀጠር ሴቶች ደጅ ይጠኗቸዋል::

ሴቶቹን የወንዶች ጥገኛ የሚያደርጋቸው አንድም የነዋይ እጥረት ወይም ደግሞ አንድን ጉዳይ ለማስፈጸም አቅም ማጣትና ያንን አቅም ወንዶቹ አላቸው ብሎ ማመን (የፋናዬ በመቶ አለቃ መደፈር ወንድሟ የደረሰበትን አፈላለገው ያገናኙኛል በሚል ነው) አለያም ደግሞ ፍቅር ነው:: ወንዶቹ ገፀባህርያት ደግሞ ሴቶቹን የሚያዩበት የየራሳቸው መነጽር አላቸው::

ምንተስኖት የተማረች መሆኗ፣ ምሁርነቷም በአጎቷ በአቶ ተገኑ ለአሰግዴ ይገለጻል:: ነገር ግን አፍላ የወጣትነት አዚም ለውብሸት ግዴለሽ አመለካከት ዳርጓት ራሷን በራሷ ስትቀጣ እናያለን:: ይህንንም ውብሸት ራሱ ይናገረዋል::

> «መጥኔ ሴቶች ሲባሉ ፍቅር የሚሉት ሞኛ ሞኝ ጨዋታ እየጎተተ ገደል የሚከታቸው ከብቶች አንዷ በሌላዋ ችግር የማትቀጣ በአፍአዊ ፍቅር በተስፋ ስጦታ የሚደለሉ ገብሶች አርቆ ማስተዋል ጠርጥሮ መመራመር የሚጎድላቸው ግልቦች እውነትም ልባቸው ከከንፈራቸው ጫፍ የተንጠለጠለ ነው የሚባለው ሀቅ ነው:: ምናልባትም ህሊናቸው ከጡታቸው ራስ የተጣበቀ ሳይሆን አይቀርም:: ወደድኩሽ ባሏት ሰሞን ሳታስተውል ትከንፋለች:: ከችግር እየሰመጠች ሕይወቷን ስታጨልመው የእድል ቀንዲሏን ስታጠቁረው ትገለፍጣለች:: የኋላ ኋላ ከእውነተኛው ሁኔታ ተዘፍቃ ስትነቃ የመረረ ልቅሶ ትነፋረቃለች::» (ቋሳ ገጽ 27)

ውብሸት እውነትም እንደእርሱ አገላለጽ ሴቶቹ ወደድኩሽ ስላላቸው ብቻ ሲንቆራጠጡ ሲለማመጡ ክብርና በራስ

መተማመናቸውን እስከሚፈታተናቸው ድረስ ሲጉላሉ ይታያሉ፡፡ ምንተስኖት ተረትታለች፡፡ ተምራ በሴቶች አይደፈር በነበረው የህግ ሙያ ዳኛ የሆነችው ህሊና መሸሻም አልቀረላትም፡፡ ፍቅሯ ተቀባይነትነት አጥቷል በውብሸት፡፡ በራሷ የምትተማመነዋና ደፋሯ ታየች አባጨፍቅም አልቀረችም፡፡ ታየች ውበሸትን አፍቅራ በሌላ ሴት ተለውጣለች፡፡ አበባየሁንም መሰል ጽዋ ሊያስጎነጫት ሲል ዝናዋን አይቶ ለወደፊት እድገቱ መሰናዘሪያ ሊያደርጋት ስላሰበ እንደሌሎቹ ሴቶች አልገፈተራትም፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የውብሸት ትምክህታዊ እምነት በዚያው መጽሀፍ ውስጥ ይመለሳል፡፡ አመላለሱ ግን ለእርሱ በሚገባው ወይም የእርሱን ጉልበት ተመጣጣኝ የሆነ አቅም ባለው ሌላ ገጸባህርይ ሳይሆን በአጋጣሚ ነው፡፡ የእጁን በእጁ ያገኛል እርሱም እንደምንተስኖት አእምሮውን ይስታል ሸባ ይሆናል፡፡ ላወለቀው ጥርስ ጥርሱን በማስወለቅ እዳውን ይከፍላል፡፡

*አንጉዝ* ላይ በአስተሳሰብ የውብሸት እኩያ የሆነው ከበደ ዋሚን ሠናይት ትቀጣዋለች፡፡ አቅዳ አስባ በመሆኑ ከምንተስኖት የተሻለ ኀብዛለች፡፡ ራሷንም ሰውታ ቢሆን ከበደን ከነአብራኩ ክፋይ ህይወቱን አጨልማዋለች፡፡ ከበደ ስለሴት ያለው አመለካከት ምን ይቋስላል? ብንል ለበለጠች ያሳያት አቀራረብ ብቻ ማንነቱን ለማሳየት በቂ ነው፡፡ ትዳር ከያዘ በኋላ ሴቲቱን በስጦታ ደልሎ ስሜቱን ሊያረካባት ይሞክራል፡፡

ለተስፋዬ ቦሩ ሴት ልጅ የወንድ መጠቀሚያ ናት፡፡ በፈለቀ አገላለጽ ሴት ርኩስ ነች (<u>ቢስ ራሔል</u>፣ 340)፡፡ ወደ ዋናዋ ገጸ ባህርይ ስንመጣ ተስፋዬ የራሔልን ውበት አይቶ 12ኛ ክፍል መጨረሷን ከረጋገጠ በኋላ እኔ ስራ አስቀጥርሻለሁ በማለት ቢሮው እንድትመጣ ያደርግና መረቡን ሲዘረጋ በነደሳለኝ አማካኝነት ትድናለች፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ከጀምስ ዊሊ ጋር የሚኖራት ግንኙነት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚያመቻቻት የተገኘውን ስራ በግሏ ሰርታ (ጉለት ከመቸርቸር በመጀመር) ትልቅ መሆን መሻቷን መሰረት አድርጎ አምባሰደር መኖሪያ ቤት በጽዳት ስራ መቀጠሯ ነው፡፡ እንዳለቸውም ይሆንላታል፡፡ በጀምስ ዊሊ አማካኝነት ፍቅሯን፣ ትልቅ ሰው የመሆን ህልሟንም ለተገፉ ሰዎች ውለታ መስራቱን ትከንበታለች፡፡

ተስፋዬን ትበቀለዋለች፡፡ ነገር ግን ለዚህ አሸናፊነት የሚያበቃት አሁንም ከክንዳምች ወንዶች የፈጠረቸው ግንኙነት ነው፡፡ ደሳለኝና ጌታሁን ባይኖሩ ከተስፋዬ ወጥመድ ማምለጧ ያጠራጥራል፡፡ ጀምስ ዊሊ ባይኖርላት አየር መንገድ ውስጥ መቀጠሯን፣ እጅግ ምናባዊ የሆነውን ትፍስህት አምባን ለመመስረት መብቃቷን እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በመሆኑም ከራሔል ጀርባ ድጋፎቿ ወንዶች ናቸው፡፡ እሾህን በእሾህ መሆኑ ነው፡፡ ኃያልነትን የተጎናጸፈችው ማህበረሰቡ ሃይልን ባጎናጸፋቸው ወንዶች ተመርኩዛ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ራሔል በምንተስኖት ሲልመሰመስ የነበረውን የበቀል ስሜት፣ በሰናይት ድፍረት አድጎ የነበረውን የበቀል ድርጊት፣ እርሷ በተሻለና በመዘረር ባለድል ሆና ስትታይ ሴቶቹ ገጸባህርያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበቱ ሲመጡ ይታያሉ፡፡ ሃይልን በሃይል ለዚያውም በአሸናፊነት ስትመክት መታየቷ የልቦለዶቹን ታሪክ ተለጣጣቂነት በሸቅብ መስመር ሂደት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በእርግጥ ከሰናይትና ከራሔል ማነው ጠንካራ? የሚል አወዳዳሪ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ራሔል ለስኬቷ የነጌታሁን ድጋፍና አስተዋጽኦ አለበት፡፡ ዓላማዋን ለሌሎች ማሳወቋ ያንን ከግብ ለማድረስ የሀሳብና የገንዘብ ድጋፍ አግኝታለች፡፡ ሠናይት

ከዚህ አኩዋያ ሲታይ ብቻዋን ነው በመስዋእትነት ጠላቷን የተጋፋችው:: ጀግናም የተሰኘችው::

ቢስ ራሔል በቀደሙት ልቦለዶች መልስ ያላገኙ ማህበራዊ ችግሮች የተፈቱበት ሆኖ ይታያል:: ለምሳሌ ተዘርተው የነበሩት ህጻናት በራሔል ድርጅት ታቅፈው ሲረዱ እናያለን (ቢስ ራሔል፣ **400**)::

***ማጠቃለያ***

ፀሐይ በልቦለዶቿ ውስጥ ለማሳየት የሞከረችው ሴቶች እንዴት ለተለያዩ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ችግሮች እንደሚጋለጡ ነው:: በዚህም ዙሪያ አብይ ስፍራ ይዞ የሚገኘው የጾታ ጦርነት ነው:: በዚህ የወንዶችና የሴቶች የጦርነት አለም፣ ጦርነቱ የሚለኮሰው ባህሉና አስተሳሰቡ ለወንዶች በሰጣቸው ስልጣንና ክንድ በሚፈጠር በደል ነው፣ ሴቶቹ በቀለኛነትእና ራስን የማገለል ስሜት ሲሰማቸው የሚታዩ ናቸው::

በታሪኮቹ ሂደት ሴቶቹን በደምሳሳው የአስተሳሰብና የኢኮኖሚ ጥገኞች ሆነው ታይተዋል:: ሌላው ቀርቶ ቀንደኛ ጠላቷ የሆነውን ከበደ ዋሚን ሠናይት ለበቀል ብትሯ ስታመቻቸው በገዛ ራሱ ንብረት በደለኛ ብላ ላዘነችባት ለአረጋሽ መኖሪያ ይሆን ዘንድ ከንግዱ ገንዘብ በመስረቅ ነው:: የራሴ የምትለው ንብረትም አልነበራትም:: ለብቻዋ ልታፈራም አትችልም ከነበረችበት ሁኔታ አንጻር::

በዚህ በጾታ ጦርነት መከከል የሚፈጠሩ ህጻናት ሲበተኑ አለያም ሲቀጩ ተስፋ ቢስ ሆነው ሲቀሩ ነው የሚታየው:: ሴቶቹ ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት በሚያደርጉት መፍጨርጨር ሁልጊዜ ወንዶች አብረዋቸው አሉ:: እነዚህ ወንዶች የሚቀርቧቸው ደግሞ ብዙውን ጊዜ ውጫዊና ውስጣዊ መልካቸውን አንብበው፣ ቀድመውም ሆነ ዘግይተው የራሳቸው ለማድረግ በማሰብ ሊሆን ይችላል::

የህጻናቱ መበተን፣ የትዳር ሁሉ መፍረስ፣ የእኩያንና የሠናያን ገጸባህርያት ጦርነት፣ ውጤቱ የሚያሳየው ልቦለዶቹ ቤተሰባዊ ተቋም ላይ ትልቅ ጥያቄ እያነሱ መሆኑን ነው::

በህትመት ቅደም ተከተላቸው ከቋሳ ወደ አንጉዝ፣ ከአንጉዝ ወደ ቢስ ራሔል ስንሄድ የድርጊት ሰንሰለታዊነት ያጋጥመናል:: ለምሳሌ መጀመሪያው ላይ ለበቀል ምኞት ብቻ ስላላት ገጸባህርይ የህይወት ጎዞ አንብበን፣ ሁለተኛው ላይ ስንመጣ የተሻለ ወኔና ድፍረት ኖሯት የበቀል ስሜቷን ስለምትወጣ ገፀባህርይ እናነባለን:: ምንተስኖትንና ሠናይትን ማነጻጻር ይቻላል::

ተደጋግመው የሚታዩ ገለጻዎች በሁለት መልኩ ስራዎቿን እንድነረዳቸው ያደርጋል:: አንደኛው አጽንኦት ለመስጠት ብላ ያደረገችው ሊሆኑ መቻሉ ነው:: ለምሳሌ መምህርነት የተናቀ ሙያ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን፣ የአእምሮ መጎዳት ሰዎች አእምሯቸው ስስ መሆኑን መልከምና ንጹህ ሆነው ሲጓዙ ሊቋቋሙት የማይችሉትን ችግር ሲጋፈጡ ህሊናቸው እንደሚናጋ፣ ይሁን እንጂ ይህንን የአእምሮ መናጋት በጥንቃቄ በማስታመም ሰዎችን ከዘለቄታዊ የአእምሮ መደንዘዝ ማዳን እንደሚቻል፣ ነጠላ እናትነት ለተማሩትም ሆነ ላልተማሩት ሴቶች ፈታኝ መሆኑን ለማሳየት፣ ሳያስቡት መከዳዳት ሰዎችን ለቂምና ለበቀል የሚያነሳሳ መሆኑን ለማሳየት ነው::

በሌላኛው ጽንፍ ደግሞ ደራሲዋ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የምታተኩረው የራሷን የህይወት ተሞክሮና ገጠመኝ ተጽእኖ ስለሚያደርግባትም ሊሆን ይችላል:: ከሁለቱ የትኛው ያመዝናል?

የሚለውን በአስረጅ ትንታኔ ለማሳየት በዝርዝር ጥናት መቃኘትና መመርመር ያስፈልጋል።

ይህን ስንል ግን አተራረክ ቴክኒክ ላይ ችግር የለም ማለት አይደለም። አሳማኝ ያልሆኑ ሰበበ አጋጣሚዎች ያጋጥማሉ። የጊዜ ፍሰት ይደነቃቀፋል። ይህ በመሆኑም ገጸባህርያቱ ሰብእና ላይ መሰናከልንና ወጥ የሆነ ሰብእና አለመኖሩን ያሳያል። ለምሳሌ ምንተስኖት ለ12 ዓመታት ሽባና የማስታወስ ችሎታዋን ያጣች ሆና የምትኖረው ልጇ የ7 አመት ሆና ሳለ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የ7 አመት ልጅ እናቷ ማን እንደሆነች የማስታወስ አቅም አታጣም። እናም ምንተስኖት የፍሬመውደድ ወላጅ መሆኗን ለማሳወቅ የነበረው የመኩሪያ ሽር ጉድና ጭንቀት አሳማኝ አይሆንም።

ፀሐይ በልቦለዶቿ አንጉል ባህሎችን ለመጋፋት ብትሞክርም አሁንም ከዘልማዳዊው እምነት ውጪ አልሆነችም። አሽናፊዋ ራሔል አሁንም በወንዶች ክንድ ውስጥ ናት። ደራሲዋ ምናልባትም ህይወት የሁለትዮሽ ትግል ውጤት መሆኗን ያሳየችበት ነው።

ሴት ልጅ ምን ጊዜም ቢሆን ለእናትነት የተፈጠረች ናት። ከዚህ ውጪ የሆኑት ግን ጨካኞች፣ አሉባልተኞች፣ ቀናተኞች፣ ናቸው እንደታሪኮቹ አካሄድ። ጸሃይ በዚህ አቀራረብ ሴት ሆኖ መፈጠር ትውልድን ለመተካት የታዘዘ መሆኑን ያሳየችበት ነው። ትውልድን ከመተካት አልፎ በሁለት እግሩ የሚቆም እንዲሆን ለማድረግ ግን ማህበረሰባዊ ኃላፊነት መሆኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አመላክታለች።

በአንጉዝ የሴት ጀግና ፈጥራለች። ደመላሽ ሴት ገጸባህርይ ቀርጻለች። ልማድንና ወግን ተገን አድርጋ ያባቷን ቃል እውን ያደረገችውን ሠናይትን ስላለች። ሥነጽሁፍ ማህበረሰባዊ መዋቅርን ይቀርጻል ሥነጽሁፍ ራሱ የኃይል መግለጫ ተቋም ነው (Literature is instutuioan of power) የሚለውን ያሳያል።

ሦስቱንም ልቦለዶች አንብበን ስንጨርስ ሁለት ሁኔታዎችን እንገነዘባለን። አንደኛው ተመሳሳይ የገጸባህርያት ሰብእና ተመሳሳይ የኩነቶች ገለጻ፣ ተመሳሳይ የህይወት ተሞክሮዎችና የገጸባህርያት እጣ ፈንታዎች ጎልተው መታየታቸው ነው። በሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ የታሪክ ተለጣጣቂነትን እናይባቸዋለን። ይህንኑ በዋና ገጸባህርያቱ አነሳስና ግብ ወይም መጨረሻ ማየት ይቻላል።

ራሔል ከሰናይት የተለየ ሰብእና ነው ያላት። የሚያመሳስላቸው ቢኖር ሁለቱም በውስጣቸወ ማንነታቸውን ለማሳየት የሰነቁት ራእይ ነው። ነገር ግን በትግል ስልት ይለያያሉ። ሰናይት ብቸኛ ናት ራሔል ግን ብዙ ወንዶች ወዳጆች አሏት። እነዳሮን (አዛውንቷ ዳርምየለሽ) የመሰሉ አዛውንት መካሪዎች አሏት።

ሴት ገጸባህርያት ተደጋጋሚ የሆነውን የህይወትን ሻከራ የሚሞርዱባቸው የተለያዩ መንገዶች አሏቸው። ፋኮ የመውጫ ስልት (ስትራተጂስ) ያላቸውን ማለት ነው። በቡና አፈላል መሰባሰብ የጠበቀ ወዳጅነት መመሥረት የራሳቸው ብቸኛ መንገዶች ሲሆኑ ቤተሰብ ላይ መጠጋት ሌላው መንገድ ነው።

እናትነት ለሚደርስባቸው ፈተና መንስኤ የሆነበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ ምንተስኖት ለእብደት አስካለ ለድህነት፣ ሽታዬ በቤተሰቦቿ ለመገለልና ለብቸኝነት፣ ፋናዬ ለዝሙት አዳሪነት ተዳርገዋል።

በመጨረሻ ማለት የሚቻለው ሴትነት ለእናትነት፣ ሴትነት ከበቀለኝነት ጋር የተያያዘ፣ ለሴት ልጅ የመጨረሻ ግቧ ትዳርና ልጅ መውለድ መሆኑን ነው ያሳየችን። እናም ደራሲዋ

**ሰፍኖ ያለውን ባህል ከመጋፋት ጋር ያለውንም የሴትን የበታችነት የሚያጸና አመለካከትም አንጸባርቃለች፡፡**

## ዋቢ መጻህፍት


**አጋረደች ጀማነህ፡፡ «የደራስያት ተሳትፎ በአማርኛ የፈጠራ ጽሁፍ ሙያ ውስጥ» በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ለማግኘ ት ከሚያስፈልጉ ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ 1979፡፡**

**ጸሀይ መልአኩ፡፡ 1982፡፡ ቋሳ፡፡ አዲስ አበባ፣ 1982፡፡**

**______________፡፡ 1984፡፡ *አንጉዙ*፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡ አዲስ አበባ፡፡**

**______________፡፡ 1996፡፡ *ቢስ ራሔል*፡፡ ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡**

Alexander, C. Jeffrey. “Cultural Pragmatics: Sociological Performance between Ritual and Strategy” in *Sociological Theory, vol. 22, no. 4.* (Dec., 2004), pp. 527-573.

Engelstad, Fredrik. “The Centrality of Power in Henrik Insen’s Dramas”. Institute For Social Research, Oslo.

______________. “The Defeat of Failure and The Failure of Success: Gender Roles and Images of the Male in Henrik Ibsen’s Last Four Plays”.

______________. 2003. “National Literature, collective Identity and Political Power” in *Comparative Studies of Culture And Power: Comparative Social Research, vol. 21.* Amsterdam. Pp. 111-145.

Foucault, Michel. “Afterward. The Subject and Power” in *Michel Foucault. Beyond Structuralism and Hermeneutics 1982 ss. 208-226.* The Harvester Press. 1982.

Franks, David D. “Power and Role-Taking. A Sociological Behaviorist’s Synthesis of Kemper’s Power and Status Model”, I (Red) Franks, D.D ^ McCarthy, E.d. in the *Sociology of Emotions*. Original Essays and Research Papers 1989 ss. 153-177. JAI Press, 1989.

Griswold, Wendy. “Recent Moves in the Sociology of Literature” in *Annual Review of Sociology, vol. 19* (1993), pp. 455-467.

Griswold, Wendy and Frederik Engelstad. “Does the Center Imagine the Periphery? State Support and Literary Regionalism in Norway and the Untied States” in *Comparative Social Research.* 1998. Vol. 17, pp.129-175.

Hilgartner, Stephen & Bosk, Charles L. “The Rise and Fall of Social Problems: A Public Arena’s

Model", in American Journal of Sciology. 94 (1). 1988. ss. 53-78.
Lamnot, Michel. "The Power-Culture link in A Comparative Perspective" in *Comparative Social Research, Volume 11*, pages 131-150. JAI Press. 1989.
Searle, John. "Creating Institutional Facts" in *The Construction of Social Reality*. Free Press: 1995.